ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

እሁድ 83ኛ ዓመት ቁጥር 076 ኅዳር 16 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






ወንጪ

# በቱሪዝም ከሀገር ውስጥ ጎብኚዎች

## ከ14 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኘ

### ለ17 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ:- በ2016 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት በቱሪዝም ከሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ከ14 ቢሊዮን ብር፤ ከውጭ ጎብኚዎች ደግሞ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን የቱሪዝም ሚኒስቴር አስታውቋል። ለ17 ሺህ ዜጎችም የሥራ ዕድል መፍጠሩ ተጠቁሟል።

የሚኒስቴሩ የኮሙኒኬሽንና የሕዝብ ግንኙነት ሥራ አስፈፃሚ አቶ አለማየሁ ጌታቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በበጀት ዓመቱ የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን ለማነቃቃት

በቱሪዝም ከሀገር ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል






«የባሕር በር የሀገር እንጂ የፓርቲ ጉዳይ አይደለም»

-አቶ ሀሰን ዳውድ
የአፋር ነፃ አውጪ ግንባር ሊቀመንበር

ገጽ 5

# በመዲናዋ የሚሰጠው የትምህርት

## እና ሙያ ሥልጠና የገበያ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ አይደለም

**እየሩስ ተስፋዬ**

አዲስ አበባ:- በአዲስ አበባ እየተሰጠ ያለው የትምህርት እና ሙያ ሥልጠና የገበያ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ አለመሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን አስታወቀ። ባለሥልጣኑ በተለያዩ ምሁራን ባስጠናው ጥናት መሠረት በከተማዋ በአብዛኛው ገበያ ተኮር ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ትምህርት እና ሥልጠና ሥርዓት የምትከተል ቢሆንም እየተሰጠ ያለው የትምህርት ሥልጠና ግን ይህንን ያካተተ አይደለም ብሏል።

ባለሥልጣኑ «ጥናት እና ምርምር ለትምህርት እና ሥልጠና ጥራት» በሚል ርዕስ ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ ጥናቱን ያቀረቡት ዶክተር ገነነ አበበ እንዳሉት በከተማዋ የሚሰጠው የቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና የገበያውን ፍላጎት የሚያሟላ አይደለም።

በተለይም በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በአምራቾች በኩል «ተማሪዎች ማሽን ይሰብራሉ» የሚል ስጋት በመኖሩ መማር

በመዲናዋ የሚሰጠው ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል



ዶክተር ገነነ አበበ



አቶ ዳኘው ገብሩ







# የኢትዮ-ጅቡቲ

## የባቡር ትራንስፖርት ከ998 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ አገኘ

ገጽ 5






ዜና

# ኢትዮጵያ የጨበጠችው «የነብር ጭራ» - አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ



ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ

# ከማዕድን ልማት በተጓዳኝ ለቁጥጥር ሥራውም ትኩረት ይሰጣል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ እየተካሄደ ካለው የማዕድን ሀብት ፍለጋና ልማት በተጓዳኝ ለቁጥጥር ሥራውም ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራ የማዕድን ሚኒስቴር አስታወቀ።

የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሁለተኛ ጊዜ የተካሄደውን ጉባኤ ሲከፍቱ እንደተናገሩት፤ የማዕድን ዘርፉ በርካታ ችግሮች ያሉበት ነው። የማዕድን ሀብት ለሀገር የሚያስገኘው ጥቅም እንዳለ ሆኖ በአግባቡ ጥቅም ላይ ካልዋለ የችግር ምንጭም ይሆናል። ከዚህ መነሻነትም ከማዕድን ልማት በተጓዳኝ ለቁጥጥር ሥራውም ትኩረት ይሰጣል።

በበርካታ የአፍሪካ ሀገራትም በዚህ ጉዳይ ግጭት ውስጥ እስከመግባት የተደረሰበት ሁኔታ መኖሩን አውስተው፤ እስከ ቅርብ ጊዜ የኢትዮጵያ የማዕድን ሀብት ለመንግሥት እንደ የገቢ ምንጭ ስለማይቆጠር በሚጠበቀው ደረጃ ትኩረት አልተሰጠውም። በዘርፉ የሚሠሩ ጠንካራ ተቋማትም አልነበሩም። የነበሩትም በቂ ትኩረት ስላልተሰጣቸው የተዳከሙ እንደነበር አውስተዋል።

በክልሎችም ቢሆን ያለውን ሀብት በሚመጥን ሁኔታ የተደራጀ ባለሙያና ተቋም አልነበረም ያሉት ሚኒስትሩ፤ በዚህም የተነሳ የማዕድን ሀብትን በአግባቡ ለመቆጣጠርም ሆነ ለማልማት ትልቅ ችግር እንደሆነ ጠቅሰዋል።

በአሁኑ ጊዜ ተቋማትን የማደራጀት፣ ማዕድናትን የማልማትና የተጠናከረ የቁጥጥር ሥርዓት የመዘርጋት ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ አመልክተው፤ የማዕድን ሀብት ላይ ቁጥጥር ሊደረግ የሚችለው በተለያዩ አካላት ቢሆንም ተጠያቂነት የሚያስከትል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ የተለያዩ ተቋማትን ያካተተ ካውንስል ተቋቁሞ ወደ ሥራ መግባቱን ገልጸዋል። ይህም ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ማዕድናት በሕጋዊ መንገድ ብቻ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚሠራ ይሆናል ብለዋል።

የማዕድን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ በበኩላቸው የማዕድን ዘርፉ በአሁኑ ጊዜ በተለየ ለቁጥጥር ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ነው ብለዋል።

የዘርፉን ልማት በአዲስ መልክ ለመሥራት ስንነሳ አንዱ የትኩረት አቅጣጫችን የነበረው የቁጥጥር ሥራው ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ለዚህም በዘርፉ ከ150 ዓመት በላይ ልምድ ካላቸው ሀገራት የልማቱን ሂደት ብቻ ሳይሆን የገጠሟቸውን ተግዳሮቶችና ለመሻገር የሠሯቸውን ሥራዎች ገምግመናል። ከዚህም ጥቅም ላይ ለማዋል ብቻ ሳይሆን ሕገ ወጥነትን በመከላከል ከምዝበራም ለመታደግ ዝግጅት እያከናወንን እንገኛለን ነው ያሉት። ይህ ተግባር በሕጋዊ መንገድ በዘርፉ ለመሳተፍ የሚመጡ ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶችም ሆነ ለውጭ ኢንቨስተሮች ትልቅ እፎይታን የሚሰጥ ነው።

በአሁኑ ጊዜም ብሔራዊ ማዕድን የልማት አስተባባሪ ኮሚቴ ተዋቅሯል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ይህም የጸጥታ መዋቅሩን፣ የፋይናንስ ተቋማትን፣ ማዕድን ሚኒስቴርንና ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት ያካተተ መሆኑን ጠቁመዋል። ይህም ኮሚቴ ከጸጥታ፣ ከፋይናንስና ከመሠረተ ልማት አኳያ ያለውን ሁኔታ የሚከታተልና ችግሮችን የሚፈታ መሆኑን አመልክተዋል።

**ተስፋ ፈሩ**

የሶፍትዌር መሐንዲሶች እንደሚገልጹት አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኮምፒዩተሮችና ማሽኖች እንደ ሰው ልጅ እንዲያመዛዝኑ፤ ነገሮችን እንዲገነዘቡ፤ ማንኛውንም ነገር እንዲማሩ፤ እንዲያቅዱና ፈጠራዎችን እንዲከውኑ በማድረግ የሚሰጣቸውን ተልዕኮ እንዲያሳኩ የሚያስችል ቴክኖሎጂ ነው።

በአፍሪካ ናይጄሪያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ኬንያ እና ግብፅ ለአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ትኩረት ሰጥተው መሥራት ከጀመሩ ሰንብተዋል። ኢትዮጵያም ከሦስት ዓመታት ወዲህ ቴክኖሎጂውን ለማሳደግ ደፋ ቀና ማለት ጀምራለች።

ወጣቱ የቴክኖሎጂ ባለሙያና በኢቢኤስ ቴሌቪዥን ከ10 ዓመታት በላይ የዘለቀ የቴክኖሎጂ ሾው አዘጋጁ ሰለሞን ካሳ እንደሚናገረው፣ ዓለማችን አራት የቴክኖሎጂ ወይም የኢንዱስትሪ አብዮት አስተናግዳለች። የመጀመሪያው ከሁለት መቶ ዓመታት በፊት ሌሎቹ ደግሞ ከዚያ መልስ የተስተናገዱ ናቸው። አራቱ አብዮቶች ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ አፍሪካውያንን አምልጠዋቸዋል።

ሰሎሞን እንደሚለው፣ አሁን ባለንበት ዲጂታል በሚባለው የቴክኖሎጂ ዘመን ማዕከላዊ ቦታ ይዞ እየዘወረ ያለው አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ቴክኖሎጂ ነው። ይሄ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ከግንዛቤ ገብቷል። በምንም ዓይነት መልኩ ቴክኖሎጂውን ወስደን ለራሳችን በሚጠቅም ሁኔታ መጠቀሙ ምርጫ ሳይሆን ግዴታ እንደሆነ በሀገር ደረጃ መረዳቱና ፍላጎቱ አለ።

«እኔ እንደ ቴክኖሎጂስት ሁልጊዜም ቴክኖሎጂው ላይ እንድናተኮር አልፈልግም። ቴክኖሎጂ እንደ መዶሻና ፒንሳ ያለ መሣሪያ ነው። በዚያ መሣሪያ ምን ዓይነት ፕሮጀክት መሥራት እንችላለን ብለን ነው መጠየቅ ያለብን» የሚለው ወጣቱ ቴክኖሎጂስት፣ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ስንል ነገርየው አይደለም ትኩረታችን፤ ዋናው ጉዳይ ቴክኖሎጂው የሚያከናውነው ነገር ነው ይላል።


ለያይዞም አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ምን ያደርግልናል? ሀገራችን ላይ ያለውን ችግር ለመቅረፍ እንዴት ያግዘናል ብለን ነው መጠየቅ ያለብን። በእርሻ፣ በጤና፣ በትምህርት፣ በመልካም አስተዳደርና በአጠቃላይ ወሳኝ በሆኑት ነገሮቻችን ላይ ሰውሠራሽ አስተውሎትን እንደ አንድ መሣሪያ ለመጠቀም መንቀሳቀስ አለብን ሲል ይመክራል።

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ዕድሜን እንደሚቀጥል፤ ከውድቀት እንደሚታደግ፣ የምግብ ዋስትናን እንደሚጨምርና በርካታ ሌሎች በረከቶች እንዳሉት የሚገልጸው ሰሎሞን፣ «መሠረታዊ በምንላቸው ዘርፎች ላይ ሁሉ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስን በረከት መጠቀም ይኖርብናል። ሁሉም ቴክኖሎጂ በጎም በጎ ያልሆነም ጎን ስላለው በታዳጊዎች ላይ የቴክኖሎጂውን በጎ ጎን ማስረጽ ይገባል» ሲል ያሳስባል።

ኢትዮጵያ ከቴክኖሎጂው በረከቶች ለመቋደስ እየሠራች በምትገኘው ሥራ ላይ ያለውን ግምገማ ሲያስቀምጥም፣ «የኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቱቲዩት ሀገራችን ከቴክኖሎጂው በትክክል መጠቀም



ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም



ወጣት ሰለሞን ካሳ

በምትችልባቸው ጉዳዮች ላይ እየሠራ ነው። ኢንስትቲዩቱ ከተመሠረተ ሦስት ዓመት ያስቆጠረ ጨቅላ ቢሆንም የአርባና ሃምሳ ዓመት ዕድሜ ያለው ተቋም የሚሠራውን ሥራ እየሠራ ነው የሚገኘው» ብሏል።

ተቋሙ ሲመሠረት ጀምሮ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) እጅ እንደነበረበት አመልክቶ፣ በቀጣይነት ከፍተኛ ሥራ እንዲሠራ ጠንካራ ክትትል እየተደረገለት እንደሚገኝ መረዳቱን ተናግሯል።

እንደ ሰሎሞን ማብራሪያ፤ ቴክኖሎጂ እንደሌላው ዘርፍ ቆሞ የሚጠብቅ አይደለም፤ ፍጥነት ይፈልጋል። ዛሬ ሠራሁና አበለጽግኩ ብሎ መኩራራትንና መቆምን አይፈቅድም። ዛሬ አዲስ የሆነው ቴክኖሎጂ በማግስቱ በተሻለ ተተክቶ ይገኛል። የዘመኑን ቴክኖሎጂ መከተል የሚያስችል ቁመና ያለው እንደ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስትቲዩት ዓይነት ተቋም ያስፈልጋል።

ወጣቱ ቴክኖሎጂስት ኢትዮጵያ ከአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በፊት ትኩረት ልትሰጣቸው የሚገባቸው ሌሎች አንገብጋቢ ጉዳዮች አሉ በሚል ከተቺዎች የሚደመጠውን አስተያየት፣ «ኢትዮጵያ ለቴክኖሎጂው ገና ነች መባል የለበትም። ገና ነን ስንል አምስተኛው የቴክኖሎጂ አብዮት ፈንድቶ ያመልጠናል። ያ ደግሞ ወደ ኋላ መቅረቱን ይበልጥ እያሰፋው ይሄዳል።» ሲል አጣጥሎታል።

የሕግ-ጠበቃና የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም በበኩላቸው፣ አሁን ዓለም የያዘችው መንገድ ወደ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ እያመራ ያለ ነው። ብዙ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ተመራማሪዎችና ፈላስፋዎች እንደሚሉት የሰው ልጅ እጅግ ወሳኝ የሆነ ጊዜ ላይ ነው የሚገኘው። አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በተያያዘው መንገድ ከቀጠለ ሰውን የመተካት ችሎታ አለው ይላሉ።

አካባቢያችንን ላንገነዘበው ወይም ላናውቀው እንችል ይሆናል እንጂ ባለንበት ዘመን ሁሉ ነገር አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ነው የሚሉት ፕሮፌሰሩ፣ «ራሳቸውን የሚያሽከረክሩ መኪናዎች ጎዳና ላይ የወጡበት ዘመን ነው። የትም ቦታ ብንሄድ ማሽኖች ከሰው ልጅ ጋር ተግባብተው አገልግሎቶችን ሲሰጡ እንመለከታለን። አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ዓለምን ተቆጣጥሯል። ግን ልብ አንለውም» ይላሉ።

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በየቀኑ በአስገራሚ ፍጥነት እያደገ በመሄዱ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሥራ ላይ ባለው የሕግ ማዕቀፍ መዳኘት የማይችልበት ደረጃ ይደርሳል የሚል ተጨባጭ ስጋት በመኖሩ አሜሪካን ሀገር ራሱን የቻለ ሕግ ይውጣለት እየተባለ መሆኑን ጠቁመው፣ «በኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ለኅብረተሳባችን የሚሰጠውን ጥቅምና ሊያመጣ የሚችለውን ጠንቅ በተመለከተ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ምሁራን ተሰባስበን ልንመክርበት ይገባል» ሲሉ ጥሪ ያቀርባሉ።

«ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) አርቆ አሳቢ ስለሆኑ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በሀገር እድገት ላይ የሚኖረውን ሚና ዛሬ ሳይሆን ከዛሬ 10 እና 15 ዓመታት በፊት የተረዱ ናቸው፤ በጉዳዩ ላይም ጽፈዋል» ያሉት የሕግ-ጠበቃና የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ፣ ኢትዮጵያ ለአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ልዩ ትኩረት ሰጥታ መሥራቷ ቅንጦት የሚመስላቸው አካላት ተሳስተዋል ይላሉ።

«መሪያችን ቀድሞን ሄዷል፤ እኛ ግን እየተጎተትን መሃል ላይ ቀርተናል» በማለትም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ለዘርፉ የሰጡትን ትኩረት ያደንቃሉ።

«በትምህርት ሥርዓታችን ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ አንድ ይዘት ሆኖ መካተት አለበት። ታዳጊዎችን በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ማሰልጠን ጥይት የጎረሰ ጠብመንጃ እንደመስጠት ስለሆነም ለበጎ ነገር እንዲጠቀሙት አድርገን ማስረጽ አለብን» ሲሉ የሚያሳስቡት ፕሮፌሰር አለማየሁ፣ የኢትዮጵያ ወጣቶች ወደ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ አዘንብለው ሀገሪቷን በከፍተኛ ደረጃ ይረዳሉ የሚል እምነት እንዳላቸው ገልፀዋል።

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ዓለማችንን የተዋወቀው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1956 ነበር። መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በአሁኑ ወቅት አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በዓለማችን ኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ድርሻ ከ350 ቢሊዮን ዶላር በላይ ደርሷል። በቀጣይም በሁሉም መስኮች ተጽዕኖው እየበረታ እንደሚሄድ ይገመታል።

# ባንኩ አጠቃላይ ሀብቱ ከአንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር በላይ መድረሱን አስታወቀ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

ሀዋሳ፡- ሲዳማ ባንክ አክሲዮን ማህበር አጠቃላይ ሀብቱ ከአንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር በላይ መድረሱን አስታወቀ። ባንኩ የባለ አክሲዮኖች 2ኛ መደበኛና 2ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤውን ትናንት በሀዋሳ ከተማ አካሂዷል።

ያለፈውን በጀት ዓመት የባንኩን አፈጻጸም ሪፖርት ለጉባኤው ያቀረቡት የባንኩ ዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ አቶ አብርሃም ማርሻሎ እንደገለጹት፤ ባንኩ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ አግኝቶ የተሟላ የባንክ አገልግሎት ለመስጠት ስኬታማ ተግባራትን አከናውኗል። በዚህም አጠቃላይ ሀብቱን ከአንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር በላይ ማድረስ ችሏል።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመትም ከ287 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ለማግኘት አቅዶ 275 ነጥብ 8 ሚሊዮን ብር ገቢ አግኝቷል ያሉት አቶ አብርሃም፤ አፈጻጸሙ የእቅዱን 96 በመቶ የሚሸፍን ነው። ከቀደመው በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸርም የ55 ነጥብ 8 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል ነው ያሉት።

በበጀት ዓመቱ 60 ነጥብ 7 ሚሊዮን ብር ትርፍ ለማግኘት አቅዶ እንደነበር አስታውሰው፤ ከ63 ሚሊዮን ብር በላይ ትርፍ በማግኘት ከእቅድ በላይ ማከናወኑን ገልጸዋል።

የባንኩ ካፒታል ከነበረበት 293 ነጥብ 3 ሚሊዮን ብር ወደ 826 ሚሊዮን ብር ማደጉን ጠቅሰው፤ የተቀማጭ ገንዘብ መጠኑም 229 ሚሊዮን ብር መድረሱን ጨምረው ገልጸዋል።

በቀጣይነትም ብሔራዊ ባንክ ያስቀመጠውን የ5 ቢሊዮን ብር የተከፈለ ካፒታል ለማሳካት ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራ አመልክተዋል።

የባንክ ኢንዱስትሪው እያደገ ከጊዜ ወደ ጊዜ ፉክክሩ እየጠነከረ መምጣቱን ገልጸው፤ ባንኩ ተወዳዳሪና ተመራጭ ሆኖ እንዲቀጥል ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል።

በዚህም ለደንበኞቹ ቀልጣፋና አስተማማኝ አገልግሎት ለመስጠት ዘመኑን የሚዋጅ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት ለማቅረብ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አስረድተዋል።

ትናንት በተካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ የዳይሬክተሮች ቦርድ እ.ኤ.አ 2022/2023 በጀት ዓመት ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት መስማትና ማጽደቅ፣ የውጭ ኦዲተሮችን እ.ኤ.አ 2022/2023 በጀት ዓመት ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት መስማትና ማጽደቅን ጨምሮ በሌሎችም አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ልዩ ልዩ ውሳኔዎችን አሳልፏል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የማዕድኑ ዘርፍ የሀገራዊ ብልጽግና ሁነኛ ዋልታ ነው!

ሀገራችን በማዕድን ሀብት ከበለጸጉ ሀገራት አንዷ ስለመሆኗ በስፋት ይነገራል። ይህንን ሀብት አውቆ ለመጠቀም በየወቅቱም የተለያየ ጥረቶች ቢደረጉም ፤ የሚጠበቀውን ያህል ከሀብቱ ተጠቃሚ መሆን አልተቻለም።

ከዚህ የተነሳም እንደ ሀገር ዕጣ ፈንታችንን በሚቀይር፤ ነገዎቻችንን ብሩህ ማድረግ በሚችል ሀብት ላይ ቆመን የድህነትና ኋላቀርነት መገለጫ ከሆኑ ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ፤ ብሄራዊ ክብራችን በሚያሳንስ የታሪክ አዙሪት ውስጥ ለመገኘት ተገድደናል።

ይህንን የሀገራችንና እና የሕዝባችን ትናንቶች መቀየር የሚያስችል ሀብት አውቆ ለማልማት ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በመንግስት ደረጃ የተለያዩ ጥረቶች እየተካሄዱ ነው። ከዚህ ውስጥም የማዕድን ዘርፉ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ መደረጉ ተጠቃሽ ነው።

በርግጥ እንደ ሀገር ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ለጀመርነው የልማት ጉዞ የማዕድን ዘርፉ ሊኖረው የሚችለው አስተዋጽኦ የማይተካ ነው። በዘርፉ ኃላፊነት በሚሰማው መንገድ መንቀሳቀስ ከቻልን ደግሞ ሁኔታዎች ከምናስበው ባለፈም ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም።

የተሻለች ሀገር ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ ከሁሉም በላይ ይህንን ሀብት በሚፈለገው ደረጃ ማወቅም፤ አልምቶ የኢኮኖሚው ዋልታ ማድረግም ተገቢ ነው። ለዚህ ደግሞ ከመንግስት ባሻገር የምርምር ተቋማትና የግል ባለሀብቱ ተሳትፎ የሚኖራቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ እንደመሆኑ፤ ይሄንኑ ሚናቸውን ማበርከት ይኖርባቸዋል።

በተለይም የምርምር ተቋማት ይህን ሀገራዊ ክፍተት በመሙላት ሂደት የሚኖራቸው አስተዋጽኦ፤ ለዘርፉ ትኩረት ከመስጠት ጀምሮ፤ ተመራማሪዎቻቸው በዘርፉ ዙሪያ ምርምሮችን እንዲያካሄዱ ማበረታታትን የሚያካትት ነው። ከዚህም ባለፈ ዘርፉን እያጋጠሙ ላሉ ችግሮች በጥናት ላይ የተመሰረቱ መፍትሄዎችን ማፈላለግ ይጠበቅባቸዋል።

ይህንን ሀገራዊ ሀብት ለማስተዋወቅም መንግሥት፣ ባለሀብቶች እና በዘርፉ የተሠማሩ የግል ሴክተሮች ድርሻቸው የጎላ ነው፤ ያሉንን አቅሞች አቀናጅተን ዘርፉን በሚፈለገው ደረጃ አልምተን ተጠቃሚ መሆን ካልቻልን የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት ጥያቄ ውስጥ መግባቱም የማይቀር ነው።

በርግጥ ሀገሪቱ የከበሩ ማዕድናት መገኛ ስለመሆኗ ከትናንት በስቲያ የተከፈተው የማዕድን ኤክስፖ ተጨባጭ ማሣያ ነው፤ ይህ እንደ ሀገር ሀብቱን አውቀን በማልማት ከድህነትና ኋላቀርነት የመውጣት እልህ ውስጥ እንድንገባ መነቃቃት ሊፈጥር የሚችል ነው። ይሄን ማዕከል በማድረግም ከሰሞኑ የማዕድን ኤክስፖ ተካሂዷል።

ይሄ ተማሪዎች፣ ተመራማሪዎች፣ ነጋዴዎች፣ ኢንቨስተሮችና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ደግሞ በዘርፉ ምን እንዳለና ምን እየተሠራ እንደሆነ በመማር ሀገራዊ ኢኮኖሚውን በአቅማቸው መጠን ማሳደግ የሚያስችላቸውን መነሳሳት ሊፈጥር የሚችል ነው።

ኤክስፖው ኢትዮጵያ ያላትን የማዕድን ክምችት የሚያሳይ፣ የማዕድን ሀብትን ወደውጭ ለመላክ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር እና ለሚቀጥለው የብልጽግና ጉዟችን መሠረት የሚጥል ስለመሆኑም በብዙ መልኩ ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም።

የምናስበው የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በኤክስፖው መክፈቻ ላይ እንዳሉት፤ በማዕድን ዘርፉ የተሰማሩ አልሚዎች በግል ማምረትና ኢንቨስት ማድረጋቸውን ማቆም ይጠበቅባቸዋል።

ከዚህ ይልቅ እንደ ሀገር በጋራ መሥራት የምንችልበትን፣ እውቀት የምናሰባስብበትንና የምንበለጽግበትን መንገድ መፍጠር ይገባል። ይህንን በአግባቡና ኃላፊነት በሚሰማው መንገድ ማድረግ ከቻልን የሀገሪቱ የብልጽግና ጉዞ መሠረት ይፋጠናል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ - አንድ ለእናቱ…!!!

በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ድምራቸው 67 የሚደርሱ አውሮፕላኖች ግዥ ለመፈጸም፤ የአውሮፕላኖቹ ምርት እንዲጀመር ከአሜሪካው አውሮፕላን አምራች ኩባንያ ቦይንግ ጋር የግዥ ትዕዛዝ ስምምነት ያደረገ ሲሆን ፤ ስምምነቱ የተፈጸመው ሁለቱም ድርጅቶች እየተሳተፉ በሚገኙበት በዱባይ የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ ዓውደ ርዕይ ላይ ነው። አሥራ አንድ የ787 ድሪም ላይነር ሞዴሎች፣ ሃያ 737 ማክስ እንዲሁም 36 ዓይነታቸው በግልጽ ያልተለዩ ጀቶች ግዥ ይፈጸማል።

አውሮፕላኖቹ ተመርተው በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ አየር መንገዱ እንደሚረከብ ሰሞኑን የወጡ ዘገባዎች ያሳያሉ። ከአፍሪካ አየር መንገዶች እስከዛሬ ይኼን ያህል ቁጥር ያለው አውሮፕላን ግዥ በአንድ ጊዜ አለመፈጸሙንና የኢትዮጵያ አየር መንገድ የመጀመሪያ መሆኑን ቦይንግ ባወጣው መግለጫ ጠቅሷል። አዳዲሶቹ አውሮፕላኖች የተሻሻሉ ሞዴሎች መሆናቸውና በውጤታማ የነዳጅ አጠቃቀም 20 በመቶ፤ የበካይ ጋዝ ልቀትንና የድምጽ ብክለት 50 በመቶ እንደሚቀንሱ ተነግሯል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአሁኑ ሰዓት 147 አውሮፕላኖች ያሉት ሲሆን፣ ከቦይንግ የታዘዙት 67ቱ በጥቂት ዓመታት ሲደርሱ ቁጥሩ በግማሽ ያድጋል ተብሎ ይጠበቃል ሲሉ የመንግስትም የግልም ሚዲያዎች በስፋት እየዘገቡ ነው። ይህ የአየር መንገዱ ስኬት አንድ ማሳያ ነው። ለመሆኑ አየር መንገዱ እንዴት ለዚህ ስኬት ሊበቃ ቻለ ወይም ሚስጥሩ ምንድነው የሚለውን በስሱ እንመልከትና ወደ አመሠራረቱ እናዘግማለን።

የኢትዮጵያን አየር መንገድን ዛሬ ለደረሰበት ስኬት ያበቃው የመጀመሪያው መሪዎቹ ባለ ራዕይ መሆናቸው ነው። ርዕያቸውን እውን ለማድረግ ደግሞ ስትራቴጂካዊ ፕላን ቀርጸው፣ የረጅም ጊዜ ርዕይ አስቀምጠው እና አየር መንገዱ ምርጥ እንዲሆን በቁርጠኝነት ሌት ተቀን መስራታቸው አየር መንገዱን ስኬታማ አድርጎታል። ሁለተኛው ደግሞ አዳዲስ አውሮፕላኖችና ቴክኖሎጂ ላይ ያለሰለሰ ኢንቨስት ማድረጉ ሲሆን፤ ሶስተኛው ከመሰሎቹ ጋር ስትራቴጂካዊ አጋርነት መመስረቱ ነው።

ሌላውና አራተኛው ለስልጠናና ለዕድገት ቁርጠኛ መሆኑ ሲሆን፤ አምስተኛ የገቢ አማራጮቹን ማስፋቱ፤ ስድስተኛው ከተለዋዋጩ ገበያ ጋር ራሱን ማላመዱ፤ ሰባተኛው ደግሞ በቡድን ስራ፣ በደንበኞች አገልግሎትና በምርጥ አሰራር የዳበረ የኮርፖሬት ባሕል ማጎልበት መቻሉ ነው ዛሬ ለደረሰበት እጅን በአፍ የሚያስጭን ስኬት ያበቃው።

ይሄን ማስጠበቅ፣ ማዝለቅና ማስፋት ይገባዋል። የሚነሱበትን ቅሬታዎች ከስር ከስር የመፍታት ባሕሉን ማጎልበትና ገለልተኝነቱን መከላከልና ማስከበርም ይጠበቅበታል። ስለስኬቱ ይሄን ያህል ሳወሳ እንደማንኛውም ኩባንያ ችግር እንዳለበት፣ ጉድለትና ውስንነትም እንደሚታይበት ዘንግቻው ፍጹም ሙሉ በኩልዬ እንዳልሆነ ጠፍቶኝ አይደለም። ስኬቱ በብዙ እጥፍ ስለሚበልጥ እንጂ።

ይልቅ የኢትዮጵያ አየር መንገድን ባሰብሁ ቁጥር ሁል ጊዜ ቁጭት የሚፈጥርብኝ አንድ ለእናቱ ሆኖ መቅረቱ ነው። እንደሱ የተዋጣላቸውና የተመሠከረላቸው አለማቀፍ አኅጉራዊና ሀገራዊ ድርጅቶች አለመፈጠራቸው ሁል ጊዜ ቁጭት ይፈጥርብኛል። የመልካም አስተዳደር፣ የግልጽነትና የተጠያቂነት ችግሮች ተደጋግመው የሚነሱባቸው የመንግስት የልማት ድርጅቶች እና ሲቪል ሰርቪሱ የአየር መንገዱን ዳና መከተል ለምን ተሳናቸው? ልዩነቱ ለምን የሰማይና የምድር ያህል ሆነ ስል እብሰከሰካለሁ።

ከአየር መንገዱ የአመራር ክህሎት መቅሰም ስንችል የመዋቅር ማሻሻያ፣ ቢፒአር፣ ቢኤስሲ፣ ካይዘን፣ ወዘተረፈ እያልን ዓለምን ብናካልልም ዛሬም ከዚህ አዙሪት ለምን መውጣት አልቻልንም ስል እጠይቃለሁ። የአየር መንገዱን ስኬት ማስፋት ወደ ሌሎች ተቋማት ማላማድ ለምን ተሳነን ስል አቤት እላለሁ። አየር መንገዱን ውጤታማ ያደረጉ አሰራሮችንና ኮርፖሬት ባሕሉን ቀምረን ወደ ሌሎች የማስፋት ነገር እንዴት የመንኮራኮር ሳይንስ ሆኖ ይቀርብናል።

**ንጉሡ ከነሚኒስትሮቻቸው፣ መኳንንቱና መሳፍንቱ፣ ዲፕሎማቶችና የሃይማኖት አባቶች ሳይቀሩ የታደሙበት ይኼ ክስተት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እጅግ እንግዳ የሆነውን ነገር ይዞ ሲመጣ ነው። ገፈርሳ ላይ በአበባ፣ በዘንባባና በሰንደቅ ዓላማ ያሸበረቁ ድንኳኖች ተዘጋጅተዋል፤ ገፈርሳ እጅግ ተሞሽራለች**

እስኪ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፤ የምርምርና የጥናት ድርጅቶች፤ ተመራማሪዎች እና የኢፌዴሪ ሲቪል ሰርቪስ ተወያዩበት እያልሁ፤ የሀገራችን ኩራት፣ የሰንደቅ ዓላማችን ሰንደቅ ስለሆነው አየር መንገድ አመሰራረትና ታሪካዊ ዳራ ላነሳሳ ወደድሁ። ብሩህ ዓለምነህ በአንድ ወቅት በአማርኛው ሪፖርተር "በታሪክ ሲቃ"የተወለደው የኢትዮጵያ አቪዬሽንና የአየር መንገዳችን በሚል ርዕስ ያጋሩትን መጣጥፍ መርጫለሁ።

‹‹በታሪክ ሲ በ1921 ዓ.ም. ነው፤ ርቀቱን አስሉት፤ ስሜቱን አስቡት! ክስተቱ እንግዳ ነው፤ ከዛሬ 87 ዓመት በፊት ክረምት ላይ። የአዲስ አበባ ሰው የክረምቱን ብርድ ለመቋቋም በተሰበሰበበት አጋጣሚ ሁሉ በከተማው ስለተናፈሰው እንግዳ ነገር ያወጋል። ቡና ሲጠጣ፣ ዕድር ላይ ሲታደም፣ ካቲካላ ቤት ሲሰባሰብ፣ እሳት ዳር ሆኖ ወግ ሲጠርቅ ሁሉ በከተማው ስለተናፈሰው ነገር ያወራል።

ስልክ ሲመጣ የሰይጣን ሥራ ነው ያለ ሕዝብ፣ መኪናን የሾርኒ ሲመለከት የነበረ ሕዝብ፣ ቴአትር ቤትን የሰይጣን ቤት ያለ ሕዝብ፣ ዛሬ ደግሞ እንኳን ለመቀበል፣ ጭራሽ ለማሰብ እንኳ ፈጽሞ የማይችለውን ነገር እንዲመለከት ቀን ተቆርጦለታል። ነሐሴ 12 ቀን 1921 ዓ.ም. የአዲስ አበባ ሕዝብ በሌሊት ተጠራርቶ፣ ኩታውንና ጋቢውን ደርቦ ወደ አንድ አቅጣጫ ይተማል። የክረምቱ ውርጭና አመዳይ፣

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

ዜና

# የኢትዮ-ጅቡቲ የባቡር ትራንስፖርት ከ998 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ አገኘ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፦ በ2016 በጀት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት 998 ነጥብ 13 ሚሊዮን ብር ገቢ ማግኘቱን የኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር አስታወቀ።

የኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ትራንስፖርት አክሲዮን ማኅበር ዋና ሥራ አስፈጻሚ አብዲ ዘነበ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሩብ ዓመቱ 63 ሺህ 81 መንገደኞችን በማስተናገድ እንዲሁም 587 ሺህ ቶን የገቢና ወጪ ጭነት በማጓጓዝ 998 ነጥብ 13 ሚሊዮን ብር ገቢ አግኝቷል።

በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 875 ሚሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ገቢው ከዕቅድ በላይ ማሳካት መቻሉን አስረድተዋል።

በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 670 ሺህ ቶን ገቢና ወጪ ጭነት ለማጓጓዝ ታቅዶ 587 ሺህ ቶን ተጓጉዟል ያሉት ዶክተር አብዲ፤ በተጨማሪም 37 ሺህ 500 መንገደኞችን ወደ ተለያዩ መዳረሻዎች ለማጓጓዝ ታቅዶ 63 ሺህ 081 በማጓጓዝ ከዕቅድ በላይ ማሳካት ተችሏል ብለዋል።



ዶክተር አብዲ እንዳመለከቱት፤ የባቡር መስመሩ በ20 ጣቢያዎች አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በቀጣይም አገልግሎት መስጫ አዳዲስ ጣቢያዎችን ለመክፈት ዝግጅት እየተደረገ ነው።

ድርጅቱ በድሬዳዋ፣ በሞጆ፣ በአዳማ፣ በለቡ፣ በእንዶዴ፣ በዲኬና በመኢሶ እንዲሁም በደወሌ የባቡር ጣቢያ መስመሮች የጭነትና የመንገደኞች የባቡር አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ ዶክተር አብዲ ተናግረዋል።

የተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍትና የአፈር ማዳበሪያ በኢትዮ-ጅቡቲ ባቡር ትራንስፖርት አማካኝነት እየተጓጓዙ መሆኑን አስታውቀው፤ በተጨማሪም የተለያዩ ተሽከርካሪዎች፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የተለያዩ ምርቶችን የማጓጓዝ አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑን ጠቁመዋል።

በቀጣይም ሲሚንቶና አሸዋ በባቡር ለማጓጓዝ ዕቅድ ተይዟል ያሉት ዶክተር አብዲ፤ ለዚህ የሚረዳ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን አንስተዋል።

እንደ ዶክተር አብዲ ገለጻ፤ ተቋሙ በአጠቃላይ ጭነት የማጓጓዝ አቅሙን ከአንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ቶን ወደ ሁለት ሚሊዮን ቶን ከፍ ማድረግ ተችሏል።

ድርጅቱ የጭነት ወጪን በመቀነስ ለተለያዩ ተቋማት ውጤታማ አገልግሎት እያቀረበ ነው ያሉት ዶክተር አብዲ፤ ከጥር ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ ከሦስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰቡን አስታውሰዋል።

እስከ 2016 ዓ.ም ታኅሣሥ ወር መጨረሻ ድረስ ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ለመሰብሰብ ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

የባቡር መስመሩ ኢትዮጵያና ጂቡቲን በማገናኘት ከወደብ ወደ መሀል ሀገር የተለያዩ ሸቀጣሸቀጦችን በማጓጓዝ ለትራንስፖርት ዘርፉ ዕድገት ከፍተኛ ድርሻ እያበረከተ እንደሚገኝ ታውቋል።

# «የባሕር በር የሀገር እንጂ የፓርቲ ጉዳይ አይደለም»

**-አቶ ሀሰን ዳውድ**
**የአፋር ነፃ አውጪ ግንባር ሊቀመንበር**

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፦ የባሕር በር ጉዳይ የሀገር እንጂ ለአንድ ወገን ብቻ የሚተው የፓርቲ ጉዳይ አይደለም ሲሉ የአፋር ነፃ አውጪ ግንባር ፓርቲ ሊቀመንበር ገለጹ። የቀይ ባሕርን ጉዳይ ፓርቲው ሙሉ ለሙሉ እንደሚደግፍ አስታውቀዋል።

የፓርቲው ሊቀመንበርና የክልሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት ሰብሳቢ አቶ ሀሰን ዳውድ የኢትዮጵያን የባሕር በር የመጠቀም ፍላጎት አስመልክተው ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ የባሕር በር አጀንዳው ሀገርን እያስተዳደረ ያለው የብልጽግና ፓርቲ አልያም የመንግሥት ብቻ ሳይሆን፤ የሁሉም ፓርቲዎችና ዜጎች ወቅታዊ ጉዳይ መሆኑን ተናግረዋል።

ሀገር ውስጥ ያሉት ተቃዋሚ ኃይሎች ጥቃቅን ነገሮችን ወደ ጎን በመተው ጉዳዩ ሊያስጨንቃቸው እንደሚገባ የተናገሩት አቶ ሀሰን፣ የቀይ ባሕር ጉዳይ የፓርቲ ሳይሆን የሀገር ጉዳይ ነው የሚለውን በተለያዩ ድጋፎች መግለጽ እንዳለባቸውም ገልጸዋል፤ ፓርቲያቸው የባሕር በር አስፈላጊነትን ጉዳይ ሙሉ ለሙሉ እንደሚደግፍም አስታውቀዋል።

«በአፋር ቀይ ባሕር ልባችን ነው የሚል አባባል አለ» ያሉት ሊቀመንበሩ፤ የአፋር ነፃ አውጪ ግንባር ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በባሕር በር ጉዳይ አጀንዳ ይዞ ሲታገል መቆየቱን አንስተዋል። ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጥያቄ ማቅረቡንም ነው ያስታወሱት።

የቀይ ባሕር ጉዳይ የተነሳንበትና እንደ ልብ ሥራችን የምናየው ጉዳይ ነው ያሉት አቶ ሀሰን፤ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ መንግሥት እየቀረበ ያለው ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ እንደ ፓርቲ ሙሉ ለሙሉ እንደሚደግፉና የአፋር ሕዝብም አጀንዳውን በግንባር ቀደምትነት የሚደግፈው ነው ብለዋል። የፖለቲካ ልዩነት ሳይኖር በወደብ ጉዳይ ላይ ሌሎች ፓርቲዎችም የሚደግፉት ነው የሚል እምነት እንዳላቸው ተናግረዋል።

እንደ ሊቀመንበሩ ገለጻ፤ ለባሕር በር ቅርብ ሆናና ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ኖሯት የባሕር በር የሌላት ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ነች። ይህ የሆነውም በቀኝ ገዢዎች ፍላጎት ላይ በተመሠረተ ደባ አማካኝነት ነው። የባሕር በር ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስፈላጊ ነው። ያለ ወደብ መኖር አስቸጋሪ ነው። በምሥራቅ አፍሪካ ላይ ሰፊውን የሕዝብ ቁጥር የያዘች ሀገር የባሕር በር ቢኖራት ጂኦፖለቲካዊ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። የአፋር ሕዝብ በሦስቱም ማዕዘናት ማለትም፤ በጂቡቲ፣ በኤርትራና በኢትዮጵያ ይገኛል። ይህ ማኅበረሰብ ተቆርጦ መኖር አይችልም። በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ የሕዝቡ የእርስ በርስ ግንኙነት ያስፈልጋል። የባሕር በር ጥያቄው ይህንንም ለመመለስ ያስችላል።

በምሥራቅ አፍሪካ የጂኦፖለቲካ ሁኔታ ያለ ወደብ መቀጠል አይቻልም በማለት፤ የባሕር በር የማግኘት መብታችን ይጠበቅ የሚለውን የመንግሥትን አቅጣጫ ሁሉም ዜጋ ያለ ልዩነት ሊደግፈው እንደሚገባ የገለጹት አቶ ሀሰን፣ አጀንዳው የሁሉም ዜጎችና የሀገር ጉዳይ በመሆኑ ከሀገር ውጪ ያሉትን ጨምሮ ሌሎችም ፓርቲዎችም ከመንግሥት ጎን በመቆም መሥራት እንዳለባቸው ጠቅሰዋል።

የምሥራቅ አፍሪካ የፖለቲካ ሁኔታ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት የባሕር በር የሌላቸው ጭምር በቀይ ባሕር ላይ



ከትመው እንደሚገኙ ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያም በዚህ መልኩ ተጠቃሚ መሆን ይኖርባታል ብለዋል። ሌሎች ከርቀት መጥተው ቀይ ባሕርን ሲጠቀሙ ኢትዮጵያ እንግዳ ሆና መቀጠል የለባትም ሲሉም ገልጸዋል። በቀጣናው ሰላምን ለማስፈንና ልማቱን ለማሳካት የባሕር በር የግድ እንደሚልና ይህንን በዲፕሎማሲ፣ በሕግና በሌሎች አስቻይ ሁኔታዎች ማስፈጸም እንደሚኖርባትም ተናግረዋል።

# በቱሪዝም ከሀገር...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በዚህም ከ14 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ገቢ ተገኝቷል፡፡

በተያዘው በጀት ዓመት ከሀገር ውስጥ ጎብኚዎች 68 ቢሊዮን ብር ለማግኘት መታቀዱን አመልክተው፤ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከስምንት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን በላይ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች 14 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ወደ ኢኮኖሚው ማንቀሳቀስ ተችሏል ብለዋል፡፡

ከሀገር ውስጥ የተገኘው ገቢ በቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዘርፍ በሚገኙ አስጎብኚ ድርጅቶች፣ ሆቴሎች፣ ባህላዊ ቁሳቁስ ሻጮችና መሰል አገልግሎት ሰጪዎችን ተጠቃሚ ያደረገ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችን እንቅስቃሴ እና ፍሰት ለመጨመር ከፍተኛ ሥራ የተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ከዚህም በሳይንስ ሙዚየም በተዘጋጀው አውደ ርዕይ ከ159 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሰዎች በሀገሪቱ የሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻዎችን ማስተዋወቅ መቻሉን አውስተዋል፡፡ ይህም የዜጎች የቱሪዝም መዳረሻዎችን የጉብኝት ባህል እያደገ እንዲሄድ የበኩሉን ሚና እንደሚጫወትም ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ከ280 ሺህ በላይ የውጭ ቱሪስቶችን በማስተናገድ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱ አቶ አለማየሁ ገልጸዋል፡፡

እያደገ የመጣው የዘርፉን ኢንቬስትመንት ከማስፋፋት አንጻር በሩብ ዓመቱ 46 የሀገር ውስጥ እና 11 የውጭ ባለሀብቶች በሆቴል እና መሰል አገልግሎት ዘርፍ መቀላቀላቸውን ጠቁመዋል፡፡

በሩብ ዓመቱ በቱሪዝም ዘርፉ ለ30 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 6 ሺህ 344 ቋሚ እና 11 ሺህ 327 ጊዜያዊ በአጠቃላይ ለ17 ሺህ 671 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል ብለዋል፡፡

አቶ አለማየሁ እንደገለጹት፤ እንደ ገበታ ለሸገር፤ ገበታ ለሀገርና ገበታ ለትውልድ የቱሪዝም መሠረተ ልማቶች የመዘርጋት እና አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን የማልማት ሥራ በስፋት መሠራቱ ለሀገር ውስጥ ብሎም ለውጭ ቱሪስቶች እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡

ይህም የሀገር ውስጥ ሆነ የውጭ ቱሪስቶች ያሉበትን አካባቢ ብቻ ሳይሆን በሀገሪቱ ተዘዋውረው የሚጎበኙአቸው መዳረሻዎች ታይተው የማያልቁ እና ሰፊ በመሆናቸው የቱሪስት መስህብ ከመሆናቸውም በላይ ቆይታ ጊዜን ለማራዘም የሚያስችሉ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

አቶ አለማየሁ አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን ከማልማት እንዲሁም ነባሮችን ከማደስ እና ከመጠገን አንጻር ውጤታማ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ገልጸው፤ በቀጣይም ዘርፉን ይበልጥ ለማነቃቃት በቱሪዝም እና በገበያ ልማት ላይ በትኩረት ይሠራል ብለዋል፡፡

የሀብት ውስንነት በዘርፉ ላይ በተለይም በዱር እንስሳት አጠቃቀም፣ ቅርስ ምዝገባ እና ጥበቃ ላይ ያሉ የሕግ ክፍተቶች የዘርፉ ተግዳሮቶች መሆናቸውን አቶ አለማየሁ አስታውቀዋል፡፡

# በመዲናዋ የሚሰጠው...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ካለባቸው ዘርፍ ውጪ ሌላ ትምህርት እንዲማሩ መገደዳቸውን ጥናቱ ማመላከቱን የጠቀሱት ዶክተር ገነነ፣ ችግሩን ለመፍታት የሕግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ባለሥልጣኑ ችግሩን ለመፍታት ለመዛኞች እንዲሁም ለኢንዱስትሪ እና ለተቋማት አሰልጣኞች ስታንዳርድ አውጥቶ በዚያ መንገድ እየተሠራ ነው ወይ? የሚለውን መከታተል እንደሚገባ የመፍትሔ ሃሳብ የጠቆሙት ዶክተር ገነነ፤ የሙያ ደረጃ፣ ሥርዓተ ትምህርት፣ የማሰልጠኛ መሣሪያዎች እና ሌሎችም ሲዘጋጁ የገበያውን ፍላጎት መሠረት አድርገው ነው ወይ ሥልጠናዎች እየተሰጡ ያሉት? ብሎ መፈተሽ እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከብቃት ምዘና ጋር ተያይዞ ከተአማኒነት እንዲሁም ከብልሹ አሠራር ጋር በተያያዘ መሻሻሎች እንዳሉ የገለጹት ዶክተር ገነነ፤ የተሠሩ ሥራዎች ቢኖሩም በቀጣይ ብዙ ሥራ መሥራት እንደሚገባ አስታውቀዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ዳኘው ገብሩ በበኩላቸው፤ ጥናቱን መሠረት በማድረግ በቅንጅት መሥራት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ባለሥልጣኑ የሥልጠናና የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ብሎም ለማገዝ በዓመት አራት ጥናቶችን ያስጠናል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ከነዚህ መካከል በ2015 የተጠናው ፍላጎት ተኮር የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና አንዱ መሆኑንም አመላክተዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ገበያን መሠረት ያደረገ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ለሀገር እድገት ወሳኝ ሲሆን፤ በቀጣይም ባለሥልጣኑ በግኝቱ መሠረት ችግሮችን ለይቶ የቁጥጥርና የድጋፍ ሥራዎችን ይሠራል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና እና አካዳሚክ ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ታደለ አየነው እንዳሉት ጥናቱን መነሻ በማድረግ ከኢንዱስትሪዎች ጋር በትብብር መሥራት ይገባል፡፡ ይህም ሠልጣኞችም ተገቢውን ትምህርት እና እውቀት ቀስመው እንዲወጡ ለማድረግ ያግዛል፡፡

## የሕይወት ገጽታ

# "ከጡረታ በኋላ ከዘራ የምንይዝበትን ስነልቦና ማስቀረት ይኖርብናል"

- አቶ ሚካኤል አልይ

በለጥሻቸው ልዑልሰገድ

ከመሃል አዲስ አበባ በምስራቁ አቅጣጫ 520 ኪሎ ሜትሮችን እንደተጓዝን የበረሃ ንግስት በመባል የምትጠራዋን እና የተለያዩ ሕዝቦች በአንድነት የሚኖሩባትና ቀደምት ስልጣኔን ከተላበሱ የኢትዮጵያ ከተሞች መካከል አንዷ የሆነችውን ድሬዳዋ ከተማን እናገኛለን። ይህች ከተማ የውጭ ዜጎችን ጨምሮ በርካቶች ከተለያየ ቦታ በመምጣት ከትመው በፍቅር ተቻችለው የሚኖሩባት ከተማ ናት።

ታዲያ በስራ ጉዳይ ወደ ድሬዳዋ ከተማ በተጓዝኩበት ወቅት በከተማዋ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የድሬዳዋ ቁጥር አንድ የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ለማየት ችዬ ነበር። በወቅቱ ከሄድኩበት የስራ ጉዳይ ባሻገር ሌላ ጉዳይ ቀልቤን ገዛኝ። ገና የጣቢያውን መግቢያ በር አልፈን ወደ ውስጥ ስንገባ ከፊት ለፊታችን የከተማዋን የበረሃ ሙቀት የሚያስረሳ ፈገግታ የተላበሱና እድሜያቸው 50ዎቹ መጨረሻ የሆኑ አንድ ግለሰብ እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ተቀበሉን። ፈገግታቸው ከልብ እንደሆነ ያስታውቃል።

ጣቢያውን እያዞሩ አስጎበኙን፤ አሁንም ትኩረቴ በእሳቸው ላይ ነው። ለአቀባበል ብቻ የመሰለኝ የፊታቸው ፈገግታ አሁንም እንዳለ ነው። እያንዳንዱን ነገር የሚያደርጉት ከልባቸው ነው። ለሚጠየቁት ጥያቄ ሁሉ ያለመሰልቸት በፈገግታ የታጀበ ምላሽ ይሰጣሉ። እኔ ከራሴ ጋር ንግግር ጀምሬያለው ከፈገግታቸው ጀርባ ያለው የሕይወታቸው ገፅ ቢገለጥ ምን አይነት ቁምነገር ይገኝበት ይሆን እያልኩ ለራሴ ጥያቄ እያቀረብኩ ነበር። በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ውስጥ ለ35 ዓመታት በትጋት መስራታቸውን ሳውቅ ደግሞ ስለእሳቸው የማወቅ ጉጉቴ ጨመረ።

እኚህ ሰው፤ በረጅም ቁመታቸው ላይ ቀጠን ያለ የሰውነት አቋም ያላቸው፤ ጥቁር የቆዳ ቀለም ተላብሰው ሙሉ ለሙሉ ነጥቶ ጥጥ የመሰለ ፀጉራቸውን በአጭሩ የተቆረጡ፤ ድሬዳዋ የሚለው ቃል በሳቸውም ሆነ ከሌላ ሰው ገና ከአንደበት ሲወጣ ፊታቸው የሚበራው፤ ቀልጣፋና ጨዋታ ወዳድ የሆኑት የድሬዳዋ ቁጥር አንድ የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ስራ አስኪያጅ አቶ ሚካኤል አልይ ሙሳ ናቸው። የዛሬው የሕይወት ገፅታ ዓምድ እንግዳችን አቶ ሚካኤል አልይ ሲሆኑ የሕይወት ተሞክሯቸውን እንደሚከተለው አዘጋጅተን አቅርበናል።

### የልጅነት ጊዜ

በምዕራብ ሐረርጌ መሰላ በምትባል ከተማ፤ ሳቃላፍቶ በምትባል የገጠር ቀበሌ ማሕበር በ1958 ዓ.ም ከአባታቸው ከአቶ አልይ ሙሳ እና ከእናታቸው ወይዘሮ ሀዋ አብዱላህ የተወለዱት አቶ ሚካኤል ለቤተሰባቸው ሶስተኛ ልጅ ሲሆኑ አባታቸው ከሶስት ሚስቶች 15 ልጆች የነበራቸው በግብርና ስራ የሚተዳደሩ ነበሩ።

በጊዜው ትምህርት የመማር እድል በጣም ትንሽ ነበር። ዘመኑ የንጉሳውያን አገዛዝ ዘመን የነበረበት በመሆኑ ሰፊ የትምህርት እድል የሚሰጠው ለባለርስት ልጆች ነበር። አቶ ሚካኤል በወቅቱ ይኖሩባት ከነበረችው መሰላ ከተማ የመማር እድል ያገኙት የጭሰኛ ልጆች ጥቂት እንደነበሩ ያስታውሳሉ። ከጥቂቶቹ መካከልም አቶ ሚካኤል አንዱ ነበሩ።


ለአቶ ሚካኤል ትምህርት ቤት ገብቶ ትምህርት መከታተል የአባታቸው ሚና ከፍተኛ ነበር። አባታቸው ልጆቻቸው ትምህርት እንዲማሩላቸው ከፍተኛ ጉጉት የነበራቸው ቢሆንም በወቅቱ ብዙ የጭሰኛ ልጆች የመማር እድልን ተነፍገው ነበር። ነገር ግን አባታቸው ልጃቸው እንዲማርላቸው ባላቸው ፍላጎት የመማር እድል ተመቻቸላቸው። ታዲያ አቶ ሚካኤል ያገኙት የመማር እድል እንዲሁ በቸርነት የተሰጣቸው አልነበረም። ከሰኞ እስከ ዓርብ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ በሳምንት ሁለት ቀን ወደ ባለርስቶቹ መኖሪያ በመሄድ የጉልበት ስራ የመስራት ግዴታ ነበረባቸው። ልጅ ስለነበሩ ጉልበት የሚያስፈልጋቸውን እንደመቆፈር እና መፍለጥ ያሉ ስራዎችን መስራት አይችሉምና በቡና ዛፎች ላይ በመውጣት ቡና ሲለቅሙ ይውሉ ነበር።

በተመቻቸላቸው የመማር እድል እዚያው መሰላ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን መከታተል ጀመሩ። በወቅቱ ትምህርት ቤቱ ያስተምር የነበረው እስከ ስምንተኛ ክፍል ብቻ በመሆኑ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመከታተል ወደ አሰበ ተፈሪ በማቅናት ጨርጨር አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመግባት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። እስከ መሰናዶ ያለውን የትምህርት ጊዜ በዚሁ ትምህርት ቤት በመከታተል ሀገር አቀፍ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወሰዱ።

የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከወሰዱ በኋላ በ1978 ዓ.ም ኮተቤ ወደነበረው እና በወቅቱ ኤሌክትሪካልና ኤሌክትሮኒክስ ኢንስቲትዩት በመባል ወደሚታወቀው የመብራት ኃይል ተቋም በመግባት ለሁለት ዓመት የዲፕሎማ ትምህርታቸው ተከታተሉ። ዲፕሎማቸውን የወሰዱት በኤሌክትሪካልና መካኒካል ቴክኖሎጂ የትምህርት ዘርፍ ሲሆን በወቅቱ ትምህርቱን የተከታተሉት 312 ምሩቃን ነበሩ።

### የስራ ሕይወት

ትምህርት ጨርሰው ዲፕሎማቸውን እንደያዙ ቀጥታ ወደ ስራው ዓለም ተቀላቀሉ። በኛ ጊዜ እንዳሁኑ ትምህርት ጨርሶ ስራ ለመፈለግ መዞር የሚባል ነገር አልነበረም የሚሉት አቶ ሚካኤል፤ ትምህርት ጨርሰን ከተመረቅን በኋላ ለስራ ምድብ እጣ ይወጣ ነበር ይላሉ። ታዲያ



**እ**ሁን ላይ ኢትዮጵያ ነዳጅ የላትም፤ ነዳጇ የኤሌክትሪክ ኃይሏ ነው። በዚህ ረገድ ደግሞ አቅሟን ለማሳደግ የአባይ ግድብን በመስራት ላይ ናት። ሕዝቦቿም በተለያየ መልኩ የግድቡን ግንባታ ሲደግፉ ቆይተዋል። ወደፊትም ይህ ተጠናክሮ ቀጥሎ በውሃም ሆነ በታዳሽ ኃይሎቿ በምታመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል ጎረቤት ሃገራት የምታዳርስና የገቢ ምንጯ ሆኖ የምትበለፅግበት ዘርፍ እንዲሆን እመኛለው ካሉን በኋላ ተሰነባብተን እኛም ወደ አዲስ አበባ ተመለስን

አቶ ሚካኤል ትውልድና እድገታቸው በምስራቁ የኢትዮጵያ ክፍል በመሆኑ ወደዛው የመሄድ ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸው። ከምስራቁ የኢትዮጵያ ክፍልም ደግሞ ድሬዳዋ ከተማን እጅግ ይወዷት ስለነበር የስራ ምድባቸው ወደ ድሬዳዋ ከተማ እንዲሆን ፅኑ ፍላጎት ነበራቸው። በወቅቱ ኤርትራም አንዷ የኢትዮጵያ ክፍል ነበረች፤ ስለዚህ ምሩቃኑ ኤርትራን ጨምሮ በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍል በእጣ መበተን ነበረባቸው።

አቶ ሚካኤልም ይህንን በልባቸው እያሰቡ ድሬዳዋ እንዲደርሳቸው እየተመኙ እጣው አወጡ። ያቺ ቀን ታዲያ ለአቶ ሚካኤል ትልቅ የደስታ እና ለአዲስ ሕይወት ጅማሮ መሰረት የሆነች እለት ሆነች። የልባቸው ፍላጎት ሰምሮ ያወጡት እጣ የናፈቋት ድሬዳዋ ከተማ ላይ አረፈ። ዛሬም ድረስ ስለዛች ቀን ሲያስታውሱ ፊታቸው የሚጋባ ደስታ ይነበብበታል።

መጀመሪያ ስራ ሲጀምሩ ደመወዛቸው 347 ብር የነበረው አቶ ሚካኤል በጊዜው በሁሉም የትምህርት ደረጃ ተለይቶ የተቀመጠ የደሞዝ እርከን እንደነበር ያስታውሳሉ። በደመወዝ እርከኑ መሰረት ለዲፕሎማ 347 ብር፣ ለዲግሪ 500 ብር፣ ለኢንጂነር 600 ብር፣ ለዶክትሬት 835 ብር ይከፈል ነበር።

ለስራ ወደ ድሬዳዋ ከተመለሱ በኋላ መጀመሪያ የስራ ገበታቸው ላይ የተገኙት በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ድሬዳዋ ቁጥር-1 የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ኤሌክትሮ ሜካኒክ በመሆን ነበር። ከጅምሩ የተመደቡት ግን በወቅቱ በሳቢያን አካባቢ በግንባታ ላይ በነበረው ድሬዳዋ ቁጥር-3 የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ነበር። የጣቢያው ግንባታ እስከሚጠናቀቅ በቁጥር-1 ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ስራቸውን እንዲጀምሩ ተደርገው የስራ ሕይወታቸው በዚሁ ጣቢያ ቀጠሉ።

ከዓመታት በኋላ መጀመሪያ ወደተመደቡበት ድሬዳዋ ቁጥር-3 የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ በመዛወር ለአምስት ዓመታት በቴክኒሻንነት ካገለገሉ በኋላ ወደ ድሬዳዋ ቁጥር-2 የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ በመግባት ለአስር ዓመታት አገልግለዋል። ከዚያ ተመልሰው መጀመሪያ ስራ በጀመሩበት ድሬዳዋ ቁጥር-1 የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ለ20 ዓመታት ያገለገሉ ሲሆን አሁንም በዚሁ ጣቢያ ስራ አስኪጅ በመሆን ጣቢያውን በመምራት ላይ ይገኛሉ። አቶ ሚካኤል በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ውስጥ ከቴክኒሻንነት እስከ ስራ አስኪያጅነት ላለፉት 35 ዓመታት አገልግለዋል።

### የትምህርት ዝግጅት ከዲፕሎማ በኋላ

አቶ ሚካኤል በዲፕሎማ ተመርቀው ያልሟት በነበረቻው ድሬዳዋ ከተማ ስራ ከጀመሩ በኋላ ወደ ሌላ ቦታ ሄዶ የመስራትን ሃሳብ ከአዕምሯቸው አውጥተው የተረጋጋ ሕይወት መስርተው መኖር ጀመሩ። ለድሬዳዋ ያላቸው ፍቅር የዲግሪ ትምህርታቸውን ላለመቀጠል እንዲወስኑ አደረጋቸው። ይህንን ውሳኔ ለምን እንደወሰኑ ሲያስረዱ "ትምህርት ብቀጥልና ዲግሪ ብይዝ የትምህርት ማስረጃዬን አስገብቼ ወደ ሌላ ቦታ እዛወራለሁ። እኔ ይህ እንዲሆን አልፈለኩም። መኖር በምፈልግበት ቦታ ቤት ሰርቼ ቤተሰብ መስርቼ ልጆች ስላፈራሁ ድሬን መልቀቅ ለኔ የሚታሰብ አልነበረም" ይላሉ።

የተወለዱት ደሬዳዋ ከተማ ባይሆንም በልጅነታቸው ብዙ ጊዜ ድሬዳዋ ይመላለሱ ስለነበር በርካታ ከድሬዳዋ ጋር የተያያዘ የልጅነት ትዝታ አላቸው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# "ከጡረታ በኋላ ከዘራ የምን...

ከ6ኛ ገጽ የዞረ

በአሰበ ተፈሪ በሚከታተሉበት ወቅት ዓርብ ከሰዓት በኋላ ከልጅነት ጓደኞቸው ጋር በእቃ መጫኛ ባቡር ተሳፍረው ወደ ድሬዳዋ ከተማ በመምጣት ቅዳሜንም እዛው በመዋል ማታ በመጡበት አመጣጥ በእቃ ባቡር ተሳፍረው ሂሳብ ሳይከፍሉ ተደብቀው ወደ አሰበ ተፈሪ ይመለሱ ነበር። በልጅነት ትንሽ ልባቸው ውስጥ ትልቅ ቦታ የነበራት ድሬዳዋ ለኑሮም ሆነ ለስራ የሚመርጧት ከተማ ሆነች። ለዚህም ነው ገና ስሟን ሲጠሩትም ሆነ በሌሎች ስትጠራ ፊታቸው ፈገግታ የሚሞላው።

በወቅቱ ድሬዳዋ የሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ በፍቅር የሚኖርባትና አሁን ቀዝቀዝ ቢልም የንግድ ማዕከል የነበረች ከተማ መሆኗን የሚናገሩት አቶ ሚካኤል፤ ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ የከተማዋ ሕዝብ አንዱ ከአንዱ ሳይለያይ ማን ምን በላ፣ ማን ምን ለበሰ ብሎ ልዩነት ሳይፈጥር በአብሮነት የሚኖርበት ሕዝብ ነው። በወቅቱ በቀኑ 12 የሚደርሱ የንግድ አውቶቢሶች ወደ ከተማዋ ይገቡ ነበር። ከፍተኛ የንግድ እንቅስቃሴ የነበረባት ከተማ በመሆኗ ደሬዳዋ ከሰባት ሰዓት በኋላ በ ሆቴሎች አልጋ ለማግኘት አዳጋች የሆነች ከተማ እንደነበረች ያስታውሳሉ።

ስለ ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

የዛሬው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ያኔ የኢትዮጵያ መብራት እና ኃይል ባለስልጣን በመባል ይጠራ እንደነበር አቶ ሚካኤል ይናገራሉ። ከዚያም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኮርፖሬሽን ወደሚለው ስያሜ ተለወጠ። ከጊዜ በኋላ ደግሞ ጥናቶች ተደርገው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ተብሎ በሁለት እንዲከፈል መደረጉንና አሁን ያለውም በዚሁ መሰረት መሆኑን ይስረዳሉ።

ዘርፉ በርካታ ስራዎች የሚሰሩበት በመሆኑ እና ሁሉንም ስራ በበቂ መልኩ ተደራሽ ለማድረግ በማለም መንግስት ተቋሙ በሁለት ተከፍሎ ሁለት የተለያዩ ግን ደግሞ ተመጋጋቢ የሆኑ ተቋማት እንዲሆኑ አደረገ። የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በመባል የተሰየመው ተቋም ከማመንጫዎች የሚመነጨውን የኤሌክትሪክ ኃይል ተቀብሎ በኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ጣቢያዎች እንዲገባ ያደርጋል። የአትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በመባል የተሰየመው ተቋም ደግሞ፤ የማከፋፈያ ጣቢያዎች ለማሕበረሰቡ የመብራት ኃይል እንዲደርስ ካደረጉ በኋላ የቆጣሪ መትከል፣ ትራንስፎርመር መትከል፣ እና የመብራት አገልግሎት ክፍያ የመሰብሰብ ስራዎችን ይሰራሉ።

ከ35 ዓመታት በፊት አቶ ሚካኤል ስራ ሲጀምሩ በድሬዳዋ ቁጥር-1 የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ የኃይል ምንጭ በመሆን ያገለግል የነበረው በነዳጅ የሚሰራ የዲዝል ጀነሬተር ነበር። አጋዴን ድረስ ሙሉ ለሙሉ የሚሸፍን የኤሌክትሪክ ኃይል ይሰጥ የነበረውም በዚሁ የዲዝል ጀነሬተር ነበር። አሁን ግን ውሀን ጨምሮ የተለያዩ ታዳሽ ኃይሎችን በመጠቀም በቂ ኃይል ማመንጨት ስለተጀመረ ዲዝል ጀነሬተሮች ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆኑ ተደርገዋል። ይህም ተቋሙ ያለፈበትን የለውጥ ሂደት የሚያሳይ መሆኑን ነው አቶ ሚካኤል የሚናገሩት።

ተቋሙ የነበረውን የሰው ኃይል እና አሁን ላይ ያለበትን ደረጃ አቶ ሚካኤል ሲያነጻጽሩ፤" ያኔ የነበረው የሰው ኃይል አነስተኛ በመሆኑና ስራ የሚከናወነው በጥቂት ሰራተኞች ብቻ ነበር፤ ጥገና የሚያስፈልጋቸው ብልሽቶች በሚያጋጥሙበት ወቅት የጥገና ባለሙያዎች ከአዲስ አበባ እስኪመጡ ይጠበቅ ነበር። አሁን ላይ ተቋሙ በቂ የሰው ኃይል ስላለው በድሬዳዋ ከተማ ያለውን ስራ በሙሉ ጥገናን ጨምሮ እዚሁ ባሉ ሰራተኞች ብቻ የሚከናወንበት አቅም ላይ ተደርሷል" ይላሉ።

**በስራ ዓለም የሚያስታውሱተ ገጠመኝ**

የሚሰሩት ስራ በቀጥታ ከኤሌክትሪክ ጋር የተያያዘ በመሆኑ በርካታ አሳዛኝ ገጠመኞችን አሳልፈለዋል። ስራው እጅግ በጣም ጥንቃቄን የሚጠይቅ በመሆኑ ከጥንቃቄ ጉድለትም ሆነ በስራ ላይ በሚያጋጥም አደጋ ሕይወትን እስከማጣት የሚያደርስ መስዋዕትነት ሊያስከፍል ይችላል። ታዲያ አቶ ሚካኤልም በሚሰሩበት ጣቢያ በአንድ ወቅት ያጋጠማቸውን ነገር መቼም እንደማይረሱትና ሁል ጊዜ ሲያስታውሱት የሚገረሙበት መሆኑን ይናገራሉ።

ነገሩ እንዲህ ነው። ከዕለታት ባንዱ ቀን እንደተለመደው አቶ ሚካኤል ዘወትር ከማይጠፉበት የስራ ገበታቸው ላይ ተገኝተው ስራቸውን እያቀላጠፉ በነረበት ሰዓት ከጣቢያው ለከተማው ነዋሪ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰጥበት መስመር በድንገት ብልሽት ይገጥመዋል። በወቅቱ መስመሩ "አማ" በመባል የሚጠራ እንስሳ ገብቶበት ትራንስፎረመሩ ፍንዳታ ስለገጠመው በጣቢያው የነበሩ የጥገና ሰራተኞችን በማስተባበር ማለዳ የተጀመረ የጥገና ስራ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ይጠናቀቃል።

በጊዜው ቴክኖሎጂም እንዳሁኑ አልተስፋፋም ነበርና መቆጣጠሪያ (ብሬከሩ) የሚዘጋውም የሚከፈተውም በእጅ የነበረ ሲሆን ብልሽቱ ባጋጠመበት ወቅት ግን መቆጣጠሪያ (ሪሞት ኮንትሮል) ተገጥሞ ገና ስራ ላይ መዋሉ ነበር። ስራውን ጨርሰው ጥገናው ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ከርቀት ሆነን እንሞክረው የሚል ሃሳብ አቀረቡ። ሁሉም በሃሳቡ ተስማምተው ከትራንስፎርመሩ ራቅ ብለው በመቆም መስራቱን መሞከር ጀመሩ። ከደቂቃዎች በኋላ ትራንስፎርመሩ ከፍተኛ ፍንዳታ አሰማ። ሁሉም በድንጋጤ ከቆሙበት ለደቂቃዎች መንቀሳቀስ አቃታቸው።

አቶ ሚካኤል ሁኔታውን ሲያስታውሱ እንዲህ ይላሉ፤ "ከዚያ ቀደም እንደምናደርገው ትራንስፎርመሩን የምናበራውና የምናጠፋው በእጃችን ቢሆን በእለቱ ጥገናውን ስንጨርስ ትራንስፎርመሩ ላይ ወጥቼ የማበራው እኔ ስለነበርኩ ዛሬ በሕይወት አልኖርም ነበር።" ይህንና መሰል አጋጣሚዎች ኤሌክትሪክ ስራ ውስጥ በርካታ ቢሆኑም ስራው አስደሳች መሆኑን አቶ ሚካኤል ይናገራሉ።

**የአመራርነት ጥበብ**

አቶ ሚካኤል ለ35 ዓመታት ያገለገሉበትን ተቋም በስራ አስኪያጅነት በማስተዳደራቸው ደስታቸው ወደር የለውም። እሳቸው የመምራትና የማስተዳደር ስራ በተቋሙ የስራ ሂደት ውስጥ ብቻ የተገደበ አይደለም። በተቋሙ ተቀጥረው ለአምስት ዓመት ከሰሩ በኋላ በውስጣቸው የኖረ የማሕበራዊ ኑሮ ፍቅር ነበርና ገና በወጣትነታቸው በምስራቅ ሪጅን የድሬዳዋ የከበቦችና የሰራተኞች መረዳጃ እድር ሊቀመንበር ሆነው ተመርጠው ኃላፊነት ተቀበሉ።

ወቅቱ የእድሩ ኮሚቴዎች እድሩን በትነው ገንዘቡን ተከፋፍለው የጠፉበት ወቅት ነበርና ሰላምን የሚወዱት መከሰስም ሆነ መከሰስ የማይፈልጉት አቶ ሚካኤል በወጣትነት ጉልበታቸው እና ባደረባቸው ቁጭት ተነሳስተው ጉዳዩን ፍርድ ቤት ድረስ በመውሰድ ፍትህ አግኝተው የተዘረፈውን የእድር ብር ለማስመለስ ቻሉ። ሃቀኝነታቸውና ለእድሩ ያላቸው መቆርቆር በብዙዎች ዘንድ ተወዳጅ ያደረጋቸው አቶ ሚካኤል በየሁለት ዓመቱ ሊቀመንበር ይቀየራል የሚለውን የእድሩን መተዳደሪያ ሕግ በፍቅር አሸንፈው ለአስር ዓመታት እድሩን በሊቀመንበርነት መሩ። በእነዚህ አስር ዓመታት ውስጥ ስለመልካም መሪነታቸው በማለት የእድሩ አባላት ሁለት ጊዜ አራት አራት ግራም ወርቅ በስጦታ አበርክተውላቸዋል።

የአቶ ሚካኤል የመምራት አቅም በዚህ ብቻ የተገደበ አልነበረም። የእድር ሊቀመንበርነታቸውን ከለቀቁ በኋላ የምስራቅ ሪጅን የሰራተኛ ማሕበርን ለ15 ዓመታት በሊቀመንበርነት መርተዋል። ጣቢያውን በስራ አስኪያጅነት ከመምራት አልፈው የሰራተኞችን እድር እና የሰራተኛ ማህበርን በዚህ መልኩ በታማኝነት በመምራታቸው የሚሰማቸውን ደስታ ሲናገሩ በኩራት ነው።

> **"አሁን ያለው ትውልድ በወረቀት ላይ ያለ እውቀት እንጂ በተግባር ሊተረጎም የሚችል እውቀት እየያዘ አይደለም፡፡ ይህ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው፤ በዚህ ከቀጠልን ነገሩ እየከበደ ይሄዳል " ይላሉ**

አቶ ሚካኤል ከስራ ሕይወታቸው ባሻገር ባለትዳርና የሁለት ወንዶችና የአንድ ሴት ልጅ አባት ናቸው። በስራው ዘርፍ ብቻ ሳይሆን በቤታቸውም ልጆቻቸውን በቀና ጎዳና እንዲጓዙ ሌት ተቀን የሚተጉ አባት ሲሆኑ ለትምህርት ትልቅ ቦታ በመስጠታቸው ሶስቱንም ልጆቻቸውን አስተምረው በዲግሪ ፕሮግራም ለማስመረቅ በቅተዋል።

ስራን አጥብቀው የሚወዱትና ዘውትር ከስራ ቦታቸው የማይጠፉት ታታሪው አቶ ሚካኤል ከመደበኛው የስራ ገበታቸው በጡረታ ለመሰናበት የሁለት ዓመት እድሜ ብቻ ቀርቷቸዋል። ስለጡረታ ሲነሳ አቶ ሚካኤል ሁሌም የሚሉት ነገር አላቸው፤ "ስራን በአግባቡ ሰርቶ በሰላም ጡረታ መውጣትን የመሰለ ነገር የለም። ጡረታ ወጣው ማለት ከስራ ዓለም እርቆ ቤት መቀመጥ ማለት አይደለም። እኔ በበኩሌ በሰራሁበት የስራ መስክ ጥሩ እውቀት አለኝ፤ ከዚህ በኋላም ብዙ መስራት እችላለሁ" ባይ ናቸው።

በሃገራችን ስለጡረታ ያለው እሳቤ እንደሚያስገርማቸው የሚናገሩት አቶ ሚካኤል፤ በሌላው ዓለም እድሜ ከስራ አይገድብም፤ እድሜያቸው ገፍቶ በእርጅና ዘመናቸው ሀገር እስከመምራት የደረሱ በርካቶች ናቸው። ይህ በኛ ሀገር ሲተገበር አይስተዋልም፤ ከጡረታ በኋላ በብዙ መስክ ሀገር የሚጠቅም እቀውቀት ይዘው ቤት የተቀመጡ ብዙዎች አሉ ይላሉ። "ከጡረታ በኋላ ከዘራ የምንይዝበትን ስነልቦና ማስቀረት ይኖርብናል" ባይ ናቸው።

"ዩኒቨርሲቲዎቻችን ብቁ የሰው ኃይል እያመረቱ አይደለም፤ ይህንን በድፍረት መናገር እችላለሁ" ይላሉ አቶ ሚካኤል ስለዩኒቨርሲቲዎች የትምህርት ጥራት ሲናገሩ። ይህንን ለማለት ያበቃቸውም ተመራቂ ተማሪዎች ለተግባር ልምምድ እሳቸው ወደሚመሩት የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ በመምጣት ሲለማመዱ ከታዘቡት በመነሳት ነው። ለልምምድ ወደ ጣቢያው የሚመጡ ተማሪዎች ትምህርቱን በንድፈ ሃሳብ እንጂ በተግባር እንዴት እንደሚሰራ የሚያውቁት ነገር የለም፤ እኛ በተማርንበት ወቅት የነበረ ተማሪ በዲፕሎማ ደረጃ ስለሚማረው ትምህርት በተግባር የተሻለ ያውቃል ሲሉ በቁጭት ይናገራሉ።

እሳቸው በተማሩበት ጊዜ የነበረውን የትምህርት ስርዓት ሲያስታውሱ አሁን ካለው የትምህርት ስርዓት በብዙ መልኩ የተሻለ መሆኑንና በንድፈ ሀሳብ ከሚሰጠው ትምህርት ጎን ለጎን የተግባር ትምህርቱንም በትምህርት ተቋማት ውስጥ ጨርሰው ይወጡ እንደነበር ይናገራሉ። አሁን ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚመረቁ ተማሪዎች ኤሌክትሪካልና ሜካኒካል ኢንጂነር ከሚለው ስያሜ በስተቀር ይዘውት የሚወጡት የተግባር እውቀት ባለመኖሩ ወደ ስራ ዓለም ከተቀላቀሉ በኋላ ሲቸገሩ ሃዘን እንደሚሰማቸው ይገልፃሉ።

"አሁን ያለው ትውልድ በወረቀት ላይ ያለ እውቀት እንጂ በተግባር ሊተረጎም የሚችል እውቀት እየያዘ አይደለም። ይህ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው፤ በዚህ ከቀጠልን ነገሩ እየከበደ ይሄዳል " ይላሉ።

**ስለኢትዮጵያ**

አሁን ላይ ኢትዮጵያ ነዳጅ የላትም፤ ነዳጇ የኤሌክትሪክ ኃይሏ ነው። በዚህ ረገድ ደግሞ አቅሟን ለማሳደግ የአባይ ግድብን በመስራት ላይ ናት። ሕዝቦቿም በተለያየ መልኩ የግድቡን ግንባታ ሲደግፍ ቆይተዋል። ወደፊትም ይህ ተጠናክሮ ቀጥሎ በውሃም ሆነ በታዳሽ ኃይሎቿ በምታመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል ጎረቤት ሃገራት የምታዳርስና የገቢ ምንጯ ሆኖ የምትበለፅግበት ዘርፍ እንዲሆን እመኛለው ካሉን በኋላ ተሰነባብተን እኛም ወደ አዲስ አበባ ተመለስን።

# አውደ ርዕዩን እንደ ትልቅ እድል የተጠቀመበት ክልል

**ዳግም ከበደ**



ባለፈው ጥቅምት ለአንድ ወር በዘለቀው የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ አውደ ርዕይ ተሳታፊ ከነበሩት ክልሎች መካከል የሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ይገኝበታል። ክልሉ በተፈጥሮ፣ ባሕል፣ ታሪክና መሰል መስህቦች የታጀቡ የቱሪዝም ሀብቶቹን ወሩን ሙሉ በአውደ ርዕዩ ማስተዋወቅ ችሏል።

እንደሚታወቀው፤ የሲዳማ ክልል የውቢቱ ሀዋሳ ከተማና የሀዋሳ ሐይቅ መገኛ ሲሆን፣ በተፈጥሮ ሀብቶች ከታደሉት የኢትዮጵያ ክፍሎች መካከል ይጠቀሳል። በኮንፈረንስ ቱሪዝም፣ በውሀ ቱሪዝምና ታላቁ ሩጫ በየዓመቱ በሚያዘጋጀው የስፖርት ቱሪዝም በስፋት ይታወቃል።

የሲዳማ ክልል የቱሪዝም መስህቦችን በርካታ ጎብኚዎች ሲመለከቱ፣ ሁለት አስጎብኚዎችም ሲያስጎበኙ ተመለከትን። ከሲዳማ ክልል የቱሪስት መስህብ አስጎብኚዎች መካከል ቅድስት አምባቸው አንዷ ናት። ቅድስት በክልሉ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ዘርፍ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ብቃት ማረጋገጫ ኦፊሰር ናት። ስለክልሉ የቱሪስት መስህቦች እንድታብራራልን የጠየቅናት ቅድስት ክልሉ እጅግ በርካታ የባሕል፣ የተፈጥሮ፣ የታሪክና ሌሎች የቱሪዝም መስህቦች ባለቤት መሆኑን ገለጸችልን፤ እንዳንዶቹን መስህቦች በስፍራው ለእይታ የቀረቡ ምስሎች በማሳየት ጭምር አብራራችልን።

እሷ እንዳለችው፤ የክልሉ መቀመጫ የሆነችው ሀዋሳ ከአዲስ አበባ በ275 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች፤ ክልሉን ለመጎብኘት ለሚፈልግ በአውሮፕላን 35 ደቂቃ በመኪና ደግሞ ከሶስት እስከ ሶስት ተኩል ሰዓት ብቻ መጓዝ ነው የሚጠበቅበት። የማረፊያ ቦታ በበቂ መልኩ ለማግኘትም አይቸገርም። በከተማዋ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች እና ሪዞርቶች በብዛት ይገኛሉና።

“በሀዋሳ ከተማ እና በሀይቅ ዳርቻዎች መቆየት የሚፈልግ በውሀ ቱሪዝም በጀልባ ሽርሽርና ስፖርት መሳተፍ ይችላል” የምትለው ቅድስት፣ ከመኖሪያ ውጪ ራቅ ብለው ለሚዝናኑ የአገር ውስጥና የውጪ ጎብኚዎች ምቹ እድል እንዳለ ትገልፃለች።

ከሀይቁ ዳርቻ ልዩ ልዩ ተግባራትን ማከናወን እንደሚቻል ገልፃ፣ ለአብነትም ጥሬና የተጠበሰ አሳ መመገብ እንደሚቻል፣ በተለይ ጥሬ አሳ መመገብን ብዙዎች እንደሚወዱት ሁሉ ብዙዎች በአግራሞት እንደሚመለከቱትም ትናግራለች። ወደ ከተማዋ የሚመጡ ቱሪስቶች በቀዳሚነት ከሚደሰቱበት ድርጊት መካከልም ከሀይቆቿ የሚገኙ አሳዎችን እየተመገቡ መዝናናት እንደሆነ አመልክታለች።

ከሀዋሳ ከተማ ወጣ ሲባል ደግሞ በወንዶ ገነት እጅግ ማራኪ ስነ ምህዳርና የተፈጥሮ መስህብ ማግኘት እንደሚቻል የምትናገረው ቅድስት፣ የወንዶ ገነት ፍል ውሃ በጎብኚዎች ዘንድ በጣም ተመራጭ መሆኑን ተናግራለች። እነዚህ ፍል ውሀዎች ከመዝናኛነትም ባሻገር ለሕክምና አገልግሎት ተመራጭ እንደሆኑም ይነገርላቸዋል። በርካታ ሰዎችም ይህን ብለው ይሄዱባቸዋል።

ከወንዶ ገነት ሳይወጣ በተፈጥሮ ቱሪዝም መዝናናት የሚሻ ቱሪስት እድሜ ጠገብ ደኖችን፣ ሌሎች እፅዋትን፣ አእዋፍትን ማግኘት እንደሚችልም ጠቁማለች፤ አካባቢው ለእፅዋትና ተፈጥሮ ምርምር ተመራጭ መዳረሻ እንደሆነ ነው ያመለከተችው። በአካባቢው የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የወንዶ ገነት ደን ኮሌጅ አንዱ የመገኘቱ ምስጢርም ይሄው ሊሆን ይችላል።

በወንዶ ገነት ሌላም የቱሪስት መስህብ ይገኛል። የቀድሞው ንጉሰ ነገስት ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ቤተመንግስት መገኛ ነች፤ በቤተመንግስቱም ንጉሱ ይገለገሉባቸው የነበሩ ቁሳቁስ ይገኛሉ፤ ከቁሳቁሱ መካከልም የሚመገቡባቸው እና ለመዝናኛነት ይጠቀሙባቸው የነበሩ ቁሳቁስ ይጠቀሳሉ። ከቤተ መንግስቱ በተጨማሪም በወንዶ ገነት ለእንግዳ ማረፊያነት የሚውል በፍራፍሬና በአረንጓዴ እፅዋት የተዋበ ሪዞርት ይገኛል።

በዳሌ ወረዳ ይርጋለም ከተማ አካባቢ ልዩ ልዩ የቱሪስት መስህቦች እንዳሉም ነው ቅድስት የጠቆመችው። እሷ እንዳለችው፤ ከእነዚህ የቱሪስት መስህቦች መካከል አረጋሽ ሎጅ ይጠቀሳል፤ ሎጁ ከከተማዋ ወጣ ባለ አካባቢ የሚገኝ ሲሆን፣ ልዩ ልዩ እጽዋት፣ የዱር እንስሳት፣ ውብ የተፈጥሮ አቀማመጥ ባለው ስፍራ ላይ ይገኛል። ይህ በበርካታ የውጭና የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች የሚጎበኝ የቱሪስት መስህብ ስፍራ መኝታ ቤቶች እና አገልግሎት መስጫዎች/ጎጆዎች/ በሙሉ የተገነቡት በቀርከሃ ነው።

የይርጋ ዓለም አካባቢ በፍል ውሀውም ይታወቃል፤ የጊዳቦ ፍልውሃ ይባላል። አንድ ጎብኚ በዚህ ስፍራ ሲገኝ በፍልውሃው ብቻ አይደለም የሚዝናናው፤ ፍልውሃው ያለበት መልካአምድር፣ እጽዋቱ፣ የዱር እንስሳቱና የጊዳቦ ወንዝ ተረጋግቶ እየወረደ ያለበት ሁኔታም ሌሎች መስህቦቹ ናቸው።

በይርጋለም አቦ ወንሾ በሚባል ወረዳ የሲዳማ “አፊኒ” ባሕላዊ የዳኝነት ስርዓት እንደሚከወን የጠቀሰችው ቅድስት፤ የሲዳማ አባቶች በዚህ ስፍራ “ሶንጎ” ተቀምጠው በአፊኒ ስርዓት እንደሚዳኙ ተናግራለች። ይህ ስርዓት የሲዳማ ብሄረሰብ ቱባ ባሕልና የጥንት አባቶች ከትውልድ ትውልድ ያሻገሩት እሴት ሳይበረዝ ሳይከለስ የሚንጸባረቅበት መሆኑን አብራርታለች።

ቅድስት እንዳለችው፤ በዚያ አካባቢ ሁሌም እሁድ ቀን ችሎት ወይም ዳኝነት የሚሰየም ሲሆን፣ የተበደለ እና ፍትህ ተነፍጌያለሁ ብሎ ያመለከተ ማንኛውም ሰው ወደ አካባቢው በመሄድ ይዳኛል። አባቶች ፍትህ ሲሰጡ ከከሳሽ ወይም ተከሳሽ ምንም አይነት ክፍያ አይደረግላቸውም።

በክልሉ ሎካ አባያ የሚባል ብሄራዊ ፓርክ እንዳለም ጠቁማ፣ በፓርኩም በርካታ ግዙፍ አጥቢ እንስሳት፣ ብርቅዬ አእዋፋት እንደሚኖሩበት ጠቁማለች። የጊዳቦ ግድብም የሚገኘው በዚሁ አካባቢ ነው። ከሎካ አባያ እስከ ነጭ ሳር በውሃ ላይ መጓዝ እንደሚቻልም ቅድስት ትገልፃለች።

ሁለት ፓርኮች የሚጋሩት ይህ ግዙፍ የአባያ ሐይቅ ከሲዳማ እስከ ጌዴኦ፣ ከኦሮሚያ እስከ ወላይታ፣ ከጋሞ እስከ ጋርዱላ የሚዘልቅ መሆኑን ታነሳለች። ከዳር እስከ ዳር 60 ኪሎ ሜትር የሚረዝመውና አንድ ሺ 162 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው የአባያ ሀይቅ የበርካታ ደሴቶች መገኛም መሆኑን ትናገራለች።

በአባያ ሀይቅ ዳርቻ ፍል ውሃዎች እንዳሉም ጠቁማለች። በአካባቢው አባያን እያየ ማደር የሚፈልግ ዳርቻው ላይ ማረፊያ አዘጋጅቶ ጉብኝቱን ማድረግ እንደሚችልም ትናገራለች።

በሲዳማ ክልል ከሚታወቁት የባሕል መስህቦች ውስጥ የደጋ መንደር ጎጆ አሰራር ስርዓትና የቡና ልማት እንደሚጠቀሱ ቅድስት ገልጻ፤ በባሕሉ መሰረት ጎጆ ቤቶቹ የሚሰሩት ከቀርከሀ ዛፍ ብቻ እንደሆነ ትናገራለች። የቡናን ምርት በተመለከተም የሲዳማ ቡና በዓለም አቀፍ ደረጃ በካፍ አፍ ኤክሰለንስ ተሸላሚ እንደሆነ በመግለፅ ቡናው ተወዳጅ ጣዕም ያለውና የክልሉ ልዩ መገለጫ ተደርጎ እንደሚታይም አስታውቃለች።

በዓለም ቅርስነት የተመዘገበው ፊቼ ጫምባላላ ሌላው የክልሉ የቱሪስት መስህብ መሆኑን ጠቅሳ፣ ፊቼ ጫምባላላ የሲዳማ ብሄረሰብ የዘመን መለወጫ መሆኑንም ነው የገለጸችው። እሷ እንዳለችው፤ የፍቼ ጫምባላላ በዓል የአሮጌው ዓመት መጨረሻ የአዲሱ ዓመት ዋዜማ እንደመሆኑ የብሄሩ ሊቃውንት የጨረቃና ኮከብ አቅጣጫና ቁጥር ተመልክተው የዘመን መለወጫው መቼ እንደሚከበር ትክክለኛውን ወርና ቀን ከወሰኑ በኋላ ለሕዝቡ በፊት ያውጃሉ።

የዘመን መለወጫ ቀኑ ከታወጀ በኋላ የብሔሩ ባሕላዊ መሪዎች (ዎማች) ለፊቼ ሳምንት ሲቀረው ከአንድ ወር በፊት የጀመሩትን ጾምና የሱባኤ (የንስሐ) ጸሎታቸውን ያጠናቅቃሉ። ሴቶች ለበዓሉ ማድመቂያ ቅቤ፣ ቆጮ፣ ወተትና ቅመማቅመም ያዘጋጃሉ። የባሕል መሪዎቹም በእለቱ ቄጣላ የሚባል እየተጫወቱ ያከብሩታል።

የፊቼ ጫምባላላ ዋዜማ ከደረሰ በኋላ የቤተሰቡ አባላትና ከብቶች በእርጥብ ቅጠል በተዘጋጀው መሽሎኪያ (ሁሉቃ/ ውስጥ ጸሐይ ስታዘቀዝቅ ሾልከው እንዲያልፉ ይደረጋል። ክብረ በዓሉም በዚሁ መልኩ ይቀጥላል ስትል ታብራራለች።

“ጫምባላላ” ዞሮ መምጣት ማለት እንደሆነ የምትገልፀው ቅድስት፤ አዲሱ ዓመት የሚጀመርበት፣ ልጆች ምንም ስራ የማይሰሩበትና እየዞሩ የሚመገቡበት፣ ከብቶች ለዚህ ቀን ተከልሎ በቆየ ጥብቅ ስፍራ ውስጥ ተለቀው የሚግጡበት ቀን መሆኑን የብቃት ማረጋገጫ ኦፊሰሯ ትናገራለች።

ልጆቹ ‹‹አይዴ ጫምባላላ›› (ዞረን መጣን) እያሉ ተሰብስበው በየአካባቢው ሲዞሩ፣ እናቶች ‹‹እሌ...እሌ..››፣ ወይም ‹‹ድረሱ....ድረሱ›› በማለት በቅቤ የተዘጋጀውን ቆጮ (ቡሪሳሜ) አቅርበውላቸው ተደስተው የሚውሉበት እንደሆነ ተናግራለች። ይህ ስርዓት ሲዳማ ካሉት ልዩ ባሕላዊ መገለጫዎች አንዱ መሆኑንም ነው የገለጸችው። ጎብኚዎች በዚህ በዓል ወቅት ወደ ሲዳማ ክልል ቢሄዱ በተወዳጁ ፊቼ ጫምባላላ ባሕላዊ ስርዓት ተደስተውና እውቀት ገብይተው እንደሚመለሱ ጠቁማለች።

የሲዳማ ብሄረሰብ ሴቶች የሚዋቡባቸው ባሕላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች እንዳሏቸውም ጠቅሳ፣ እነዚህም የጎብኚዎችን ትኩረት እንደሚስቡ ቅድስት ገልጻለች። ከእነዚህ መካከልም “ጉመይ” በመባል የሚታወቅ የእጅ አምባር፣ አንገት ላይ የሚደረግ “ባእላቶ” እንደሚገኙበት ትናገራለች።

የብቃት ማረጋገጫ ኦፊሰሯ ቅድስት እንዳብራራችው፤ የሲዳማ አባቶችም ከነሀስ የተሰሩ የጀግንነታቸው መገለጫ የሆኑ የአንገትና የእጅ አምባሮችን ያደርጋሉ። አባቶች ይህንን ጌጥ ሲያደርጉ ጦርነት መርተው ጀግንነት ሰርተው እንደነበር ያስታውሳሉ፤ በዚህም ክብርን ያገኙበታል። ሌላው አባቶች በፊቼ ጫምባላላ ክብረ በዓል ቀን ከጉማሬ ቆዳ የተሰራ ጋሻ እንዲሁም በተመረጠ እንጨትና ብረት የተሰራ ጦር ይዘው በበዓሉ በሚከበርበት አደባባይ ጉዱማሌ እንደሚወጡም ታስረዳለች።

“በክልሉ በቱሪስት ማረፊያነት የሚገኙ ሆቴሎች፣ ሎጆችና ሪዞርቶች ባሕላዊ ምግቦችን በራሳቸው ተነሳሽነት ያቀርባሉ” የምትለው ቅድስት፣ አንድ ጎብኚ በሲዳማ ክልል ሲገኝ የክልሉን ማሕበረሰብ ባሕላዊ ጣፋጭ ምግብ አንደ “ቦርሳሜና ጩካሜ” ያሉትን መመገብ እንደሚችልም ትናገራለች። ይህም ሲዳማንና ማሕበረሰቡን ይበልጥ ለማወቅ የባሕል ትስስር ለመፍጠር እንደሚረዳው ታስረዳለች።

ቅድስት በአውደ ርዕዩ በርካታ ሺህ ጎብኚዎች የሲዳማ ክልል የቱሪስት መስህቦችን ማስጎብኘት መቻሉን ጠቅሳለች። ለአንድ ወር የክልሉን መስህብ በሚፈለገው ልክ ማስተዋወቅ መቻሉን ነው የተናገረችው።

ሲዳማ በቅርብ ጊዜ የተመሰረተ ክልል እንደመሆኑ መሰል አውደ ርዕዮች የቱሪዝም ሀብቶችን ለማስተዋወቅ እንደሚረዱ ጠቅሳ፣ ክልሉ ይህን መድረክ ማግኘቱ ትልቅ እድል መሆኑን የብቃት ማረጋገጫ ኦፊሰሯ ቅድስት አስታውቃለች። የሲዳማን ባሕል፣ ታሪክ፣ ተፈጥሮና ልዩ ልዩ ሀብቶች በሚፈለገው ልክ የማያውቁ እንደሚኖሩ ገልፃ፣ በመድረኩ ሲገኙ እነዚህ ሰዎች እድሉን እንዲያገኙና ክልሉ ያለውን ሀብት ተረድተው ለመጎብኘት እንዲነሳሱ ለማስተዋወቅ እድል ማግኘቱን ገልጻለች።

ቅድስት እንዳለችው፤ መድረኩ የሲዳማ ክልል የቱሪዝም ሀብቶችን ለማያውቁት ከማስተዋወቅ ባሻገር፣ ክልሉ ከአቻ ክልሎችና ከልዩ ልዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ከመጡ የዘርፉ ተቋማት ጋር ትውውቅ ለማድረግና ልምድ ለመለዋወጥም ረድቶታል። መሰል መድረኮች አንደ ሀገርም እንደ ክልልም በቀጣይም ቢዘጋጁ የአገር ውስጥ ጎብኚዎችን ጨምሮ ዓለም አቀፍ ቱሪስቶች የኢትዮጵያን የቱሪዝም ሀብቶችን የበለጠ እንዲያውቁ ለማድረግ ይረዳል። ይህ ሲሆን በቱሪዝም ዘርፉ የሚፈለገው ለውጥ እንደሚመጣ ተናግራለች።

ከመስከረም 29 እስከ ጥቅምት 28-2016 ዓ.ም በቆየው የሳይንስ ሙዚየም የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ አውደ ርዕይ ላይ በርካታ የቱሪዝሙ ዘርፉ ተዋንያን ተሳትፈዋል። አውደ ርዕዩን በአካል 170 ሺህ የሚጠጉ በዲጂታል አማራጭ ደግሞ 9 ሚሊዮን አካባቢ የሚደርሱ ጎብኚዎች እንደተመለከቱት መረጃዎች ጠቁመዋል። በአውደ ርዕዩ ተሳታፊ ከሆኑ ተጋባዦች መካከል የሁሉም ክልሎች ባሕልና ቱሪዝም ቢሮዎች ይገኙበታል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## የ60ዎቹ ግድያ

**ዋለልኝ አየለ**

ስያሜውን ያገኘው በሁለት ምክንያት ነው። የመጀመሪያው እና ዋናው የተገደሉት ሰዎች 60 መሆናቸው ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ ዘመኑ በ1960ዎቹ መሆኑ ነው። ይህ ክስተት በጥቅሉ በተለምዶ የ60ዎቹ ግድያ እየተባለ ይጠራል። የተገደሉት ሰዎች ሲቆጠሩ 59 ናቸው የሚሉ የታሪክ ፀሐፊዎችም አሉ፤ ሆኖም ግን ቁጥሩን በማጠጋጋት ይመስላል «60ዎቹ» እየተባለ ነው የሚጠራው።

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን 49 ዓመታትን ወደኋላ መለስ ብለን በዚህ ሳምንት ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም በደርግ መንግሥት የተፈጸመውን የ60ዎቹን ግድያ እናስታውሳለን። ከዚያ በፊት ግን እንደተለመደው በዚህ ሳምንት የተከሰቱ ዓለም አቀፍና የአገር ውስጥ የታሪክ ክስተቶችን እናስታውስ።

ከ90 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 11 ቀን 1926 ዓ.ም ጋዜጠኛ፣ የታሪክ ፀሐፊ እና ደራሲ ጳውሎስ ኞኞ ተወለደ።

ከ60 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 13 ቀን 1956 ዓ.ም (ኖቬምበር 22 ቀን 1963) 35ኛው የአሜሪካ ፕሬዚደንት የነበሩት ጆን ፊዝጀራልድ ኬኔዲ (ጆን ኤፍ ኬኔዲ) ተገደሉ። ጆን ኤፍ ኬኔዲ በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የነበሩ ሲሆን በኢትዮጵያ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያለው ቤተ መጻሕፍት በስማቸው (ኬኔዲ ላይብረሪ) ይጠራል።

ከ18 ዓመታት በፊት ኅዳር 13 ቀን 1998 ዓ.ም አንጌላ ሜርክል የጀርመን የመጀመሪያዋ ሴት መራሂተ መንግሥት ሆነው ተሾሙ። ሜርክል ለ16 ዓመታት ያህል የጀርመን መራሂተ መንግሥት ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተው ከ16 ዓመታት በኋላ ከታኅሳስ 2014 ዓ.ም ጀምሮ ለኦላፍ ሾልዝ ለቀዋል።

ከ137 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 14 ቀን 1879 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ ተቆረቆረች። እቴጌ ጣይቱ ፍል ውሃ ፊል ፊል ወደሚልበት መስክ ወርደው ሳሉ፤ ከዚህ በፊት አይተዋት የማያውቋት አንዲት ልዩ አበባ አይተው ስለማረከቻቸው ቦታውን «አዲስ አበባ» ብለው በመሰየማቸው የአዲስ አበባ ከተማ መነሻ መሆኑ በታሪክ ይነገራል።

ከ27 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 14 ቀን 1989 ዓ.ም 175 መንገደኞችን አሳፍሮ ከአዲስ አበባ ወደ ናይሮቢ በመጓዝ ላይ የነበረው፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ ቁጥር ET961 የመንገደኞች አውሮፕላን፣ በሦስት ኢትዮጵያውያን ጠላፊዎች ተጠልፎ በኮሞሮስ ደሴት ላይ ተከሰከሰ፤ በአደጋው ጠላፊዎቹን ጨምሮ 125 ሰዎች ሞቱ።

ከ49 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 15 ቀን 1967 ዓ.ም 3 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዓመት ዕድሜ እንዳለው የሚነገርለት የ«ድንቅነሽ» (ሉሲ) ቅሪተ አካል በኢትዮጵያ፣ አፋር ውስጥ ሐዳራይቶ በሚባል ቦታ ተገኘ። ቅሪተ አካሉን (አፅሙን) ያገኙት ፕሮፌሰር ዶናልድ ካርል ዮሃንሰን የተባሉ አሜሪካዊ የቅሪተ አካል ጥናት ባለሙያ ናቸው። ቶም ግሬይ የተባለና በወቅቱ የድህረ ምረቃ ተማሪ የነበረ የቅሪተ አካል ጥናት ባለሙያም የፕሮፌሰር ዶናልድ ዮሃንሰን ረዳት ሆኖ ይሰራ ነበር።

ከ7 እና 3 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ኅዳር 16 ቀን እንደሚዋደዱ የሚነገርላቸው ጓደኞችና ወዳጅ የነበሩት፤ ሁለቱ የዓለማችን ተፅእኖ ፈጣሪ ሰዎች፣ ኩባዊው አብዮተኛ ፊደል ካስትሮ እና አርጀንቲናዊው የእግር ኳስ ተጫዋች ማራዶና ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩበት ነው። ፊደል ካስትሮ ኅዳር 16 ቀን 2009 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ከአራት ዓመት በኋላ ህዳር 16 ቀን 2013 ዓ.ም ደግሞ አርጀንቲናዊው ዲዮጎ አርማንዶ ማራዶና ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

አሁን በዕለቱ በዝርዝር ወደምናየው የ60ዎቹ ግድያ ታሪክ እንሂድ።

ለሺህ ዘመናት የኖረውን ንጉሣዊ ሥርዓት በመጣል አዲስ አብዮት የፈጠረው ወታደራዊው የደርግ መንግሥት ሙስና እና ሌብነትን አጥብቆ በመፀየፍ፣ ከምንም በላይ ደግሞ በቆራጥ አገር ወዳድነቱ ሥርዓቱን የታገሉት ጠላቶቹ ሳይቀር ይመሰክሩለታል። «ባለአባት» በሚል ኋላቀር አስተሳሰብ የጌታ እና ሎሌ ሥርዓት የነበረበትን ገርስሶ መሬትን ለአራሽ ገበሬ በመሥጠቱ በድሃው ማህበረሰብ ሲመሰገን ኖሯል።

በእነዚህ ሁሉ ጥሩ ሥራዎቹ ውስጥ ግን ስሙ በመጥፎ እንዲነሳ ያደረጉት ጥቁር ታሪኮች አሉት። ከእነዚህ የደርግ ታሪኮች አንዱ እና ዋነኛው የ60ዎቹ ጀኔራሎችና ከፍተኛ ባለሥልጣናት ግድያ ነው። «አብዮት ልጆቿን በላች» እየተባለም ይገለጻል።

ክስተቶቹን ለማስታወስ፤ የፍሰሐ ያዜን «የኢትዮጵያ የአምስት ሺህ ዓመት ታሪክ ቅጽ 2» መጽሐፍ፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ (የተለያየ ዓመት ዕትም) እና የሌተናል ኮሎኔል ፍስሃ ደስታ «አብዮቱና ትዝታዬ» መጽሐፍ ምንጮቻችን አድርገናል።

ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶም የደርግ ሊቀ መንበር ሆነው ከተሾሙ ጊዜ ጀምሮ በደርጉ አባላት መካከል መስማማት አልነበረም። ይባስ ብሎ ወደለየለት ስድድብና አተካራ ውስጥ ገቡ። ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያምም ስለ ጀኔራል አማን ጉዳይ ለመወያየት የደርጉን አባላት ሰበሰቡ። ከዚሁ ጎን ለጎንም ከአንደኛው ብርጌድ ስድስተኛ ክፍለ ጦር የተውጣጡ ወታደሮች ጀኔራል አማንን በቁጥጥር ስር እንዲያውሉ ቢታዘዙም «እንዴት አማንን በሚያህል ጀግና ላይ አፈሙዝ እናነጣጥራለን? ... አናደርገውም!» ብለው እምቢታቸውን ገለፁ።

በዚህ ምላሽ ክፉኛ የደነገጠው ደርግ ጦሩ አፈሙዙን ወደ ደርግ ሊያዞር እንደሚችል ስጋት ቢገባውም የመጣው ይምጣ በማለት በቅርብ የተገኙ የደርግ ጥበቃ ኮማንዶዎችን ከጥቂት የቡድኑ አባላት ጋር በማጣመር በሻለቃ ዳንኤል አስፋው መሪነት ወደ ጀኔራል አማን መኖሪያ ቤት ላከ። ጀኔራል አማን እጅ እንዲሰጡ ቢጠየቁም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ከነ ሻለቃ ዳንኤል ጋር ተኩስ ገጠሙና የተወሰኑትን ገድለው በመጨረሻ ተገደሉ።

ከደርግ አባላት ጋር ስብሰባ ተቀምጠው የነበሩት ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም የጀኔራሉን መገደል ሲሰሙ አጀንዳውን በቁጥጥር ስር ወዳሉት የንጉሰ ነገሥቱ ባለስልጣናት ጉዳይ አዞሩት። (እርሳቸው ግን በደርግ አባላት ተገድጄ ነው አጀንዳውን ያነሳሁት ብለዋል)

«አማን አንድ ወታደር ነው፤ የእርሱ ጉዳይ ትልቅ አጀንዳ አይደለም፤ ይልቅ የነዚያን ደም መጣጮች ጉዳይ ዳር ሳናደርስ ከዚህ አዳራሽ አንወጣም» ያሉት ንዑስ የደርግ አባላት ደርግ በቁጥጥር ስር ያዋላቸው የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ መንግሥት ባለስልጣናት ስማቸው እየተጠራ «በለው ... ይገደል ... ይሙት ...» በሚል የወታደሮች ፍርድ የስብሰባው አዳራሽ ድብልቅልቁ ወጣ።

ብዙዎችን አስገርሞና አሳዝኖ የነበረው «በለው ... ይገደል ... ይሙት ...» ሲሉ የነበሩት ንዑስ የደርግ አባላት ብዙዎቹን ታሳሪዎች በስምም በመልክም የማያውቋቸው መሆኑ ነው። በእርግጥ ብዙዎቹ ታሳሪዎች በሙስና የነቀዙ ግለሰቦች እንደነበሩ የታሪክ ፀሐፍት ያስረዳሉ። ነገር ግን ለኢትዮጵያ ሀገራቸው የደከሙ እንደነ አክሊሉ ሀብተወልድ ያሉ ብርቅዬ ሰዎችም ከታሳሪዎቹ መካከል ነበሩ። በሙስና የነቀዙት ግለሰቦች ክስም ቢሆን ጉዳያቸውን ለመመርመር በተቋቋመው መርማሪ ኮሚሽን በኩል መጣራት ይገባው ነበር የሚሉ ብዙዎች ናቸው።

እንግዲህ በዚህ ዓይነቱ አሳዛኝና አስደንጋጭ ውሳኔ 52 የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ባለስልጣናትና 8 የደርግ አባላት(ባለስልጣናት) ሞት ተፈረደባቸውና ተገደሉ።

በነገራችን ላይ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም «ትግላችን» በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ስለ ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶም በሚያትተው ርዕስ፤ ጥፋቱን ወደ ጀኔራሉ ወስደውታል። እርሳቸው የሚሉት፤ ጀኔራሉ ኤርትራን ለማስገንጠል ሲያሴሩ ደርሸባቸዋለሁ ነው። በአንድ ስብሰባ ላይም ኤርትራን ለማስገንጠል እንደሚሰሩ በግልጽ የተናገሩት ነው ብለው የጀኔራል አማን ሚካኤል አምዶን ንግግር በመጽሐፋቸው ላይ በጥቅስ ውስጥ አድርገው አስፍረዋል።

ያም ሆነ ይህ አብዮት ልጆቿን ትበላለች የሚለው እውን ሆና የጦር ልምድ፣ የዲፕሎማሲ ልምድ እና የፖለቲካ ልምድ ያላቸውን ሁሉ የአብዮቱ ሰይፍ አረፈባቸው።



እነዚህ 60 የጦር መኮንኖች እና ከፍተኛ ባለሥልጣናት የተገደሉት በተለያየ ምክንያት ነው። ኃይላቸውን ከሕግ አግባብ ውጭ ተጠቅመዋል በሚል ውንጀላ የተገደሉ ባለስልጣናት ጸሃፊ ትዕዛዝ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድን ጨምሮ 17 ናቸው። ስልጣናቸውን ከሕግ አግባብ ውጭ ተጠቅመዋል በሚል ውንጀላ ደግሞ 34 ባለሥልጣናትና የጦር መኮንኖች ተገድለዋል፤ አብዛኞቹ የጦር መኮንኖች ናቸው።

«የእርስ በእርስ ጦርነት ለመቀስቀስ በተሸረበ ደባ እና ታላቁን የለውጥ እንቅስቃሴ ለመግታት በተደረገ አሻጥር» በሚል 5 የተገደሉ ሲሆን ሦስቱ ካፒቴን ናቸው። «ለመስሪያ ቤት የተገባን ቃል ኪዳን ባለመጠበቅ እና በጦር ኃይሉ ውስጥ ክፍፍል ለመፍጠር ሙከራ ማድረግ» በሚል ውንጀላ ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶምን ጨምሮ ሦስት ሰዎች ተገድለዋል።

ጸሐፊ ትዕዛዝ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ በደርግ ታጣቂዎች ከመገደላቸው ቀደም ብለው በዕለቱ (ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም) እንዲህ ብለው ነበር። «እኛን በመግደል ኢትዮጵያን ከድህነቷ የምታወጧት ከሆነ፣ ድርጊታችሁን እንደ ታላቅ በረከት በፀጋ እንቀበላለን» ከዚያ በኋላ ኢትዮጵያ ከድህነት ወጣች ወይ? የሚለውን ለታሪክ ፍርድ እንተወው!

ባለሥልጣናቱ የተከሰሱበት ጉዳይ ሳይነገራቸው ክስ ሳይመሠረትባቸው ለወራት በእስር ቆይተዋል። ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም ግን የደርግ አባላት እና ንዑስ ደርግ በመባል የሚታወቁ በታላቁ ቤተ መንግሥት ተሰበሰቡ። በስብሰባው የደርጉ ተቀዳሚ ሊቀመንበር ጀነራል አማን አንዶም ግን አልተገኙም።

በባለሥልጣናቱ ላይ አንዳችም ክስ ሳይመሠረትባቸው ደርግ ራሱ ከሳሽ ራሱ ፈራጅ ሆኖ ሥልጣኑን ተጠቅሞ በዚሁ ቀን በስብሰባ የግድያ ውሳኔ አሳለፈባቸው። በ60ዎቹም የቀድሞ ባለሥልጣናት ላይ የግድያ እርምጃው የተወሰደው ከርቸሌ ተብሎ በሚታወቀው እስር ቤት ግቢ ውስጥ ሲሆን፣ አስከሬናቸውም እዚያው እንዲቀበር ተደርጎ ዘመድም እንዳይጠይቅ ተከልክሏል።

በዚህ እርምጃ ሁለት ጠቅላይ ሚኒስትሮችን ጨምሮ አገረ ገዢዎች የካቢኔ ሚኒስትሮችና የጦር ጄኔራሎች ያለፍርድ ውሳኔ ነው የተገደሉ። «ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም» ሲል የነበረው ደርግ በትረ ሥልጣኑን እንደጨበጠ «በደም ተጨመላለቀ» የሚል ወቀሳ ሲሰነዘርበት ኖረ።

ግድያውን አስመልክቶ የተለያዩ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል። የሌተናል ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ትዝታዎች በሚል ገነት አየለ በጻፉት መጽሐፍ ላይ የግድያ እርምጃውን ለመውሰድ አስቀድሞ የተያዘ አጀንዳ እንዳልነበር ኮሎኔል መንግሥቱ ገልጸዋል። «ማንም አመነም አላመነም እኔ የምናገረው እውነቱን ነው፤ በበኩሌ የተወሰደውን እርምጃ አልደገፍኩትም፤ ሌሎችም የደርግ አባላት በስልሳዎቹ ግድያ ሊጠየቁ አይገባም፤ ምክንያቱም በተቆጡ በተናደዱ የንኡስ ደርግ አባላት ድምጽ ተውጠን በዚያ ውስጥ ተዘፍቀን የተላለፈ ውሳኔ በመሆኑ። እኛ የተነሳንለትና ቆመንለት የነበረው ዓላማ ይሄ አልነበረም። ያንን የመሰለ ውሳኔ ለመወሰን አላሰብንም ነበር።» ብለዋል። የዚያን እለት ብቸኛው አጀንዳ የጀነራል አማን ጉዳይ እንደነበረም ጠቅሰው፣ ስለ ኃይለስላሴ መንግሥት ባለሥልጣኖች የሚል ነገር ጨርሶ አልነበረም ተብሏል። ችግሩ ኮሎኔል መንግሥቱ በዚያ ጉዳይ ላይ «አድርገነዋል» ይላሉ ወይ የሚለውን የማመን አለማመን ጉዳይ ነው።

በደርግ ዘመን ምክትል ፕሬዚዳንት የነበሩት ፍስሃ ደስታ «አብዮቱና ትዝታዬ» በሚል መጽሐፋቸው እንዳሰፈሩት፤ ኮሎኔል መንግሥቱ ጉባዔውን በሊቀመንበርነት መምራት ብቻ ሳይሆን አጀንዳውን አዘጋጅተው አቅርበዋል ሲሉ ጽፈዋል። ኮሎኔል መንግሥቱ ኅዳር 13 ቀን 1967 ዓ.ም የእስርና የአብዮታዊ እርምጃ ደብዳቤ ጽፈዋል። በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ስምና ፊርማ የተጻፈው ይህ ደብዳቤ «በቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣናት ላይ የተላለፈውን ከፍተኛ የፖለቲካ ውሳኔ ተግባራዊ ስለማድረግ ይመለከታል» በሚል የተጻፈ ነው።

በዚሁ ደብዳቤ ለ54 ሰዎች መቀበሪያ ጉድጓድ እርምጃው በሚወሰድበት ቦታ በዶዘር እንዲቆፈር ታዝዟል፤ እርምጃው የሚወሰድባቸው ባለሥልጣናት ዝርዝርም ተለይቷል። ኮሎኔል መንግሥቱ እንዳሉት ሳይሆን በእስረኞቹ ላይ ውሳኔ ለማሳለፍ ነው ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም ስብሰባ የተካሄደው።

ከጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ በመጀመር የካቢኔ ሚኒስትሮች፣ ጠቅላይ ገዥዎች፣ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ባልደረቦች፣ የንጉሡ ባለሥልጣናት ስማቸው ሲጠራ ተሰብሳቢዎቹ በወሬ ወይም በአሉባልታ የሰሙትን እየተናገሩ ድምጽ መስጠቱ ቀጠለ። ሃምሳ ዘጠነኛው ተራ ሲደርስ በቃ የሚል ስለተሰማ ሰብሳቢው ለዛሬ እዚህ ላይ እናበቃለን፤ የቀሩ ካለ ሌላ ጊዜ ይታያል በማለት የድምጽ መስጠት ሂደት ቆመ ሲሉ በመጽሐፋቸው አስፍረዋል።

ያም ሆነ ይህ ሁሉም ያመኑት ነገር ቢኖር 60ዎቹ መገደላቸውን ነው። የተገደሉት ሰዎች ደግሞ በየዘርፉ ልምድ እና እውቀት የነበራቸው ናቸው። እንዲህ አይነት ታሪኮችን ስናስታውስ ዋና ቁም ነገሩ ከስህተቶች ለመማር ነው፤ አኩሪ የሆኑ የአባቶቻችንን ጀግንነትና ጥበብ ደግሞ እንድናስቀጥላቸው ነው። እንደ ዓድዋ፣ ጉራዕ፣ ጉንደት፣ ካራማራ የመሳሰሉ የድል ታሪኮቻችንን በኩራት ስንናገራቸው እንደ ሰገሌ ጦርነት እና የ60ዎቹ አይነት የእርስበርስ ግድያዎችን ደግሞ ከስህተቶቻችን እንድንማርባቸው ነው። ምክንያቱም የ60ዎቹ ግድያ የደርግን ታሪክ ጥላሸት ቀብቶታል።

በአኩሪ ታሪኮቻችን እንኩራ፤ ከስህቶቻችን እንማር !

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

# የአባቷ ጌጥ - ሲቲያና

ቤዛ እሸቱ

ጋሽ ቴኒ ቦንገር፤ የቤታቸው የበኩር ልጅ ሆና የመጣችውን ድንቡሽቡሽ ሕጻን ልጅ ተመልክተው፤ ጌጥ እንደምትሆናቸው በመተማመን ስሟን ሲቲያና ሲሉ ሰየሙት። በጉራጊኛ የኔ ጌጥ እንደማለት ነው።ዳሩ ምን ያደርጋል ጌጤ ነሽ ሲሉ ያወጡላትን ሥም ትርጉሙ ሳይገባት ቀረና 'አመለ' ስትል ለራሷ ባወጣችው ሥም ለወጠችው።ለረዥም ጊዜያት መጠሪያዋ ይሄው ሥም ሆኖ ቆይቷል።ለዚህም ነው፤ አመለ በሚለው ሥሟ ይበልጥ የሚያውቋት የቅርቦቿ ሁሉ 'ኤሚ' በሚል የቁልምጫ ስም የሚጠሯት። ነገር ግን፤ ከልጅነት ወደ እውቀት ስትሸጋገር በማንነት ፍለጋ ውስጥ አባቷ ያወጡላትን ሲቲያናን መልሳ ያገኘችው ይህቺው ድምጻዊት፤ የዛሬው የዝነኞች ገጽ ምርጫችን ሆናለች። ድምጻዊቷ፤ በረዥም ጉዞ ውስጥ በርካታ ውጣ ውረዶችን አልፋ በቅርቡ "ማንነቴን" የተሰኘ የአልበም ሥራ ለአድማጭ ጆሮ ለማድረስ በቅታለች።

ድምጻዊት ሲቲያና ቴኒ ቦንገር ውልደትና ግማሽ የልጅነት ዘመን እድገቷ ቢሾፍቱ ከተማ ውስጥ ነበር። ሰላማዊ የልጅነት ሕይወትን በዚያው አሳልፋለች። ገና በጊዜ ሙዚቃ መስማትና መሞከርም ትወድ ነበር። በአቅራቢያዋ ያሉ ሁሉ ድምጿ እንደሚያምር አስተያየት ሲሰጧትና ከሌሎች ልጆች በተለየ እንድትዘፍን ሲጋብዟት፤ እሷም የተለየ ነገር እንዳላት ብትረዳም ብዙም ቁብ አልሰጠችውም ነበር።እያደር በሙዚቃ ፍቅር ይበልጥ እየተለከፈች ሄደች።ስለሙዚቃ ምኑም ሳይገባት ያንንም ይሄንንም ትሰማለች፤ የሰማችውንም ታንጎራጉረዋለች። የነገ ሕይወቷ በትምህርት እንደሚለወጥ የሚያምኑት ቤተሰቦቿ አንዳችም ሳይሰስቱ ለትምህርቷ አስፈላጊውን ሁሉ ያሟሉላት ነበር። እሷም ብትሆን ጎበዝ ተማሪ ነበረች።ታዲያ ይህ የዘለቀው ሙዚቃ እስኪያሸፍታት ድረስ ብቻ ነበር። ልቧ በሙዚቃው በተረታ ጊዜ ሀሳቧ ሁሉ ማን አልበም አወጣ...ከየትኛው ሙዚቃ በኋላ የትኛው ተከተለ...የሚለውን መያዝ እንዲሁም ግጥምና ዜማ መሸምደድ በመሆኑ የትምህርት ጥናት ጊዜዋን ተሻማው።በዚህም ከቤተሰቦቿ ጎሽ!...ከሚል ድጋፍ ይልቅ "ምነው ትምህርትሽን እንዲህ በሸመደድሽ!" የሚል ተደጋጋሚ ተግሳጽ አስተናግዳለች።እናት፤ ልጇ ሙዚቀኛ እንድትሆን ምንም ሀሳቡም ፍላጎቱም የላትም።አባቷ ግን፤ እሷ ባትሰማውም ቢያንስ ተምረሽ ያሬድ ጊቢና የተማረ ሙዚቀኛ ሁኚ የሚል ሀሳብ ነበረው።

ሲቲያና የ14 ዓመት ታዳጊ ሳለች ከቤተሰቦቿ ጋር መኖሪያቸውን ከቢሾፍቱ ወደ ወልቂጤ ከተማ ቀየሩ። ኑሮዋን በወልቂጤ ካደረገች በኋላ፤ በአንድ ወቅት የዞኑ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ወጣቶችን እንደየፍላጎታቸው ለማሰልጠን ማስታወቂያ ያወጣል።ሥልጠናው በውዝዋዜ፣ በድምጽ፣ በትወና እንዲሁም የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋቾችነት ሲሆን፤ በመረጡት ዘርፍም መሰልጠን የሚቻል ነበር። እሷም እንደ ጊዜ ማሳለፊያ በአቋራጭ ከምትወደው ሙዚቃ ጋር መገናኛ ይሆናት ዘንድ፤ ከያሬድ የሙዚቃ ትምህርት ቤት በመጡ ምሩቃን የሚሰጠውን የድምጽ ሥልጠና መከታተል ጀመረች።ለሦስት ወራት ያህል ተብሎ የተጀመረው ሥልጠና አስር ወራትን አስቆጠረ።ያኔ ከአሰልጣኞቿ የምታገኘው ማበረታቻ ይበልጥ ትክክለኛ መንገድ ላይ መሆኗን አመለከታት።በትምህርት ቤት ውስጥ በሚኒ ሚዲያና መሰል ክበባት ያገኘችው የሙዚቃ እውቀት ይበልጥ እንዲዳብር መንገድ ተመቻቸላት።በሕይወቷ ውስጥም የበርካታ ድምጻውያንን ሙዚቃ እያደመጠችና ሥራቸውን እየሞከረች ቆይታለች። ከሁሉም በላይ በሙዚቃ የይቻላል መንፈስን ያጎናጸፋት ድምጻዊ ግን፤ ፋሲል ሽመልስ ነው።ድምጻዊው የመጀመሪያ አልበሙን ሲያወጣ እድሜው 12 ነበር።ህጻኑ ሙዚቀኛ እየተባለ በሁሉም ዘንድ መነጋገሪያ በሆነበት ወቅት እሷ ደግሞ 14 ዓመቷ ነበርና የ12 ዓመት ልጅ አልበም ካወጣ እኔም ማድረግ እችላለሁ የሚል ስሜት በውስጧ ዳበረ።ያኔ ታዲያ እናቷ ምን ሲደረግ! አሉ፤ አባቷ ግን ተምረሽ በወጉ ያሬድ ገብተሽ ሙዚቃን ትማሪያለሽ አሏት። እሷም "ሌላው በ12 ዓመቱ አልበም ይሠራል እኔ ምን ሲደረግ ገና እስከ አስረኛ ክፍል እማራለሁ" አለች።

የ14 ዓመት ታዳጊ በነበረችበት በዚሁ ጊዜ ክለብ ውስጥ ሙዚቃን ትጫወት ነበር።ቤተሰቦቿ አይሆንም ሲሉ ለሙዚቃው ከነበራት ጥልቅ ፍቅር የተነሳ ከቤት እስከመጥፋት ደርሳለች። እድሜዋ ከፍ ሲል ግን ቤተሰቡ፤ ከመቀበል ውጭ እሷና ሙዚቃን መነጠል የማይታሰብ መሆኑ ገባው።በዚህ ሁኔታ እሷና ሙዚቃ በነጻነት መቀራረብ ሲጀምሩ መላው ቤተሰብ ከሀገር ወጣ።መኖሪያዋ ከሀገር ውጭ በደቡብ አፍሪካ ጆሀንስበርግ ከተማ ሆነ።በስደት ሕይወቷ ያገኘችውን ሥራ ትሰራለች፤ የተሻለ ገቢም ታገኛለች።ነገር ግን ውስጧ ሰላም፤ ደስታ ይሉት ነገር ጠፋ።ያኔ የምወደውን ሙዚቃ ብሰራ ልቤ ይረጋል ስትል አሰበች።እናም በ2001 ዓ.ም "ዝም አትበል" የተሰኘ የመጀመሪያ ነጠላ ዜማዋን በኦዲዮ ብቻ አወጣች።በሥራው ምንም እንኳን ገቢ ባታገኝበትም ከሰላሟ ጋር ተገናኘች።ሙዚቃ ይሄን ያህል ደስታ ከሰጠኝ በሚል በሙዚቃ ሥራዋ ገፋችበት።"የኔ ጀግና" የተሰኘ ሁለተኛ ነጠላ ዜማዋን ደገመች። የቪዲዮ ክሊፑ እንደነገሩ በደቡብ አፍሪካ ስለተሰራ ያን ያህል ሕዝቡ ጋር አልደረሰም ትላለች። ሙዚቃ የውስጧ ሠላም ሰጪ ነውና፤ በመሃል ለእረፍት ወደ ሀገሯ ስትመጣ ለአልበም ይሆኑኛል ብላ ያሰበቻቸውን ግጥምና ዜማዎችን ሰብስባ ሄደች። እዛው እያለች ከሌላው ሕይወቷ ጎን ለጎን ግጥምና ዜማ ስታጠና ቆየች።የወሰደችውን ግጥምና ዜማ ተለማምዳ ጨረስኩ ብላ ስታስብ በድምጽ ለመቀዳት ወደ ሀገሯ ለመምጣት ማቀድ ያዘች።በሷ ሀሳብ የቀራት ስቱዲዮ ገብቶ ማቀናበር ብቻ ነበር።የሚያውቁ ሰዎች ለዚህ ስድስት ወር ብቻ እንደሚበቃት ነገሯት።እሷም ከደቡብ አፍሪካ በኢትዮጵያ የስድስት ወራት ቆይታ አድርጋ አልበሟን ለማጠናቀቅ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ በሻንጣዋ ሸክፋ ወደ ሀገሯ ኢትዮጵያ መጣች።

የአልበም ሥራዋን ለማጠናቀቅ የስድስት ወራት ቆይታ ብቻ በቂ እንደሆነ አስባ ብትመጣም፤ ነገሩ እንኳንስ ለአልበምና ለነጠላ ዜማ እንኳን የሚሆናት አልነበረም። አልበም ጨርሼ እመለሳለሁ ያለችባቸው ስድስት ወራት በስቱዲዮ ወረፋ ብቻ እንደቀልድ ወደመጠናቀቅ ተቃረቡ። በዚህ መሃል እሷም ተስፋ ወደመቁረጡና ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመመለስ ሻንጣዋን ወደማዘጋጀቱ ተሸጋገረች።የስድስት ወር ቆይታዋ ያለስኬት ተጠናቆ መኖሪያዋ ወደሆነው ደቡብ አፍሪካ ልትመለስ መሆኑን የተረዳው የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋች ጓደኛዋ፤ ኤልያስ መልካ ጋር ልውሰድሽና እዛ ሞክሪ ሲል ከኤልያስ ጋር አገናኛት።በስቱዲዮው ውስጥ ያገኘችው ኤልያስ መልካ የሰበሰበቻቸውን ሳምፕሎች ሰምቶ ሲያበቃ "ይሄ ለሆነ ሰው የተዘጋጀ ግጥምና ዜማ ነው፤ መጀመሪያ አንቺን እንፈልግሽና ለአንቺ የሚሆን ግጥምና ዜማ እናዘጋጅ" ሲል በአዳዲስ ግጥምና ዜማዎች ሥራው ሀ ተብሎ ተጀመረ።ለአልበም ሥራዋ የሚሆኑ ሙዚቃዎችን እዚያው ተመርጦ መዘጋጀቱ ይበልጥ ምቾት ሰጣት።ሆኖም ግን ኤልያስ ፈላጊው ብዙ ነውና በዚህ የተነሳም ስቱዲዮ ለመግባት ወረፋው ከባድ ሆነባት። አንድ ዙር ስቱዲዮ ለመግባት ረዥም ጊዜ መጠበቅ የግድ ነበር። በዚህ መሃል ወደ ደቡብ አፍሪካ ሄድ መለስ እያለች፤ ለአልበም የሚሆኑ ሙዚቃዎቿ ቁጥር ከዓመት ወደ ዓመት መጠናቸው እየጨመረ ሄደ። ኤልያስ ጋር በቅንብሩ ሰበብ ሲገናኙ በመሀል ተግባቡ። ሲያወሩ የምታነሳቻቸውን ሀሳቦች ግጥም አድርጎ ያቀርብላታል።በዚህ መልኩ ከቅንብር በዘለለ አዲስ ግጥምና ዜማ እየተፈጠረ ለሰባት ዓመታት ያህል ቆይተዋል። የአልበሟ መጠሪያ የሆነው "ማንነቴን" በዚህ አይነት ሂደት የተፈጠረ ነበር።

ሲቲያና ለረዥም ጊዜያት በደቡብ አፍሪካ የቆየች ስለሆነ፤ በኢትዮጵያ ቆይታዋ እየተመለከተች የነበረውን የሴት ልጅ አያያዝ እንግዳ እየሆነባት ግራ ተጋብታም ነበር። ኤልያስም፤ አብዛኛውን ጊዜውን ለሙዚቃ ሥራው የሰጠና በስቱዲዮ የተወሰነ ስለነበረ ስለከተማው እንቅስቃሴ ብዙም መረጃው አነበረውም። እሷ ወጣ ብላ ባየችው ነገር አንዳንዴ እየተገረመች አንዳንዴም እንዴት ይሆናል? እያለች በንዴት ስሜቷን ታካፍለዋለች።እርሱም፤ ከዚህ ጨዋታቸው መሃል ከሲቲያና ያገኘውን ሀሳብ "ማንነቴን" ሲል በግጥም ከተበው።ዘፈኑ ሴት ልጅ ሴትነቷን እና ቁንጅናዋን ለሌላ ነገር መተላለፊያ እንዳታደርገው ታስቦ የተሰራ ነው።የአልበም ሥራውን ከመጀመሯ በፊት በሠራቻቸው ሁለት ነጠላ ዜማዎች ላይ፤ ከአልበም ሥራው ጎን ለጎን ሌላ ሦስት ሙዚቃዎችን በማከል፤ ከአልበሟ ውጭ አምስት ነጠላ ዜማዎችን ለመሥራት ችላለች። "አጉላባይ" የተሰኘው ነጠላ ዜማዋ አልበሙ ወደማለቁ እየተቃረበ ነው ተብሎ ስለታሰበ ለአልበሙ ማስታወቂያነትም እንዲያገለግል ታስቦ የተለቀቀና አልበሙ ውስጥ ሊካተት የታሰበ ሥራ ነበር።በወቅቱ ሲቲያና ነብሰጡር ስለነበረች እንዲሁም ኤልያስም ሕመሙ እየተባባሰበት በመሄዱ አልበሙ ይወጣል ተብሎ በታሰበው ጊዜ ሳይወጣ ቀረ።

"ወለባ" በቪድዮ ክሊፕ የተሠራላት ሌላው ነጠላ ዜማዋ ነው።ወለባ በግጥምና ዜማ ብስራት ሱራፌል በቅንብሩ ደግሞ ታምሩ ማሞ ተሳትፈውበታል።"መልሰው" የተሰኘው ነጠላ ዜማ ማንነቴ የተሰኘው አልበሟ ከመውጣቱ በፊት የወጣ የመጨረሻ ነጠላ ዜማዋ ነው።አራቱ ነጠላ ዜማዎቿ በድምጽና ምስል፤ በክሊፕ መልክ የተሠሩ ናቸው። ስድስት ወራት ብቻ በቂ ናቸው ብላ የጀመረችው የአልበም ሥራ እንደቀልድ አስር ዓመታትን ፈጅቷል። የቅንብር ሥራው በኤሊያስ ተጀምሮ እንዲያልቅ ቢታሰብም፤ ነገር ግን ኤሊያስ ከቅንብሩ ባሻገር በአውታር መተግበሪያና ተዛማጅ የቅጂ መብቶችንም በማስጠበቅ ዋነኛ ተንቀሳቃሽ እንደመሆኑ፤ ጊዜ በማጣትና ጤናው ከዕለት ወደ ዕለት እየታወከ በመሄዱ በሥራው ሌሎች አቀናባሪዎችንም ለማካተት የግድ ሆነ።"ማንነቴን" በተሰኘው አልበሟ ውስጥ 14 ዜማዎች የተካተቱ ሲሆን፤ ኤልያስ መልካ በግጥምና ዜማ እንዲሁም በቅንብር በስድስቱ ተሳትፎባቸዋል።የሌሎቹን ስድስት ሥራዎች ቅንብር በአቤል ጳውሎስ የተሠሩ ሲሆን ቀሪዎቹ ሁለት ሙዚቃዎች ደግሞ በካሙዙ ካሳ ተቀናብረዋል።በዜማ ደረጃ ኤልያስ መልካን ጨምሮ አብነት አጎናፍር፣ ጃሉድ አወል፣ ብስራት ሱራፌል አበበ፣ አንተነህ ወራሽና ካሳሁን እሸቱ የራሳቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል።በግጥም ሥራው አሁንም ኤልያስ መልካ፣ አብነት አጎናፍር፣ መሰለ ጌታሁን፣ ወንደሰን ይሁብ፣ ካሳሁን እሸቱ አሻራቸውን አኑረዋል።በሥራው ላይ እያሉ የአልበሙ የጀርባ አጥንት የነበረው የኤሊያስ መልካ ድንገተኛ ሞት ነገሮችን ይበልጥ አክብደኋቸው ነበር።እሷም ለጊዜው ልረፍ ስትል ሥራዎቿን ሰብስባ ወደ ደቡብ አፍሪካ ተመልሳ መሄዷ አልቀረም።

በስድስት ወር አጠናቅቀዋለሁ ብላ የገባችበት የአልበም ሥራ አስር ዓመት ቢፈጅባትም አልበሙ ተጠናቀቀ ስትል፤ ሌላው ያላሰበችው አድማጭ ጋር ማድረሱ ራሱን የቻለ አድካሚና አሰልቺ ሂደት የነበረው መሆኑን ነው።ከብዙ አሰልቺ ጉዞ በኋላ ለእያንዳንዱ ሥራ ክፍያ መፈጸምና እንዲሁም ማስተዋወቁ የእርሷ ድርሻ መሆኑን ስትረዳ ሥራዋን ይዛ ወደ ደቡብ አፍሪካ ተመለሰች።በሙዚቃ ኢንዱስትሪ ውስጥ ባለው ሂደት ተስፋ ቆርጣ ወደ መተው በተሸጋገረችበት ወቅት ነበር ሰዋሰው መልቲሚዲያ ወደ ሥራ የገባው።የሷን ሙዚቃ ካቀናበሩት አንዱ የሆነው አቤል ጳውሎስ ለሰዋሰው አጭቶ ሥራዋን አስደመጣቸው፤ የሠራችውን ሥራ ስለወደዱት አልበሟን ገዙት።ይሄን ሁሉ መስዋዕትነት የከፈለችበት የሙዚቃ አልበሟ በሰዋሰው መተግበሪያ በኩል ለአድማጮች ቀርቧል።መተግበሪያው አዲስ ከመሆኑና እሷም ለአድማጮች አዲስ ከመሆኗ አንጻር ጥሩ አቀባበል እንዳገኘች ታምናለች።መተግበሪያው እየታወቀና እየተለመደ ሲመጣ አልበሟ ከዚህ በላይ እንደሚደመጥ ተስፋ ታደርጋለች።

በአልበሟ ሥብጥር ውስጥ ታስቦበትና ምን ቢተላለፍ ይሻላል ተብሎ የተካተቱ ሥራዎች እንዳሉ ሁሉ "ብርድ ብርድ አለኝ" የሚለው ሥራዋ በአጋጣሚ የተካተተ ነበር።ሲቲያና፤ ወደ ካሙዙ ስቱዲዮ ለሥራ መጥታለች።ሆኖም ካሙዙ ስቱዲዮ ውስጥ ከሌላ ድምጻዊ ጋር ሥራ ላይ ነበሩ።በሰዓቱ ዝናብ ነበር፤ የሚጥለውን ዝናብ ተከትሎ ብርዱ ኃይለኛ ነው።ድምጻዊ ጃሉድ፣ ድምጻዊ ብስራት እና ሲቲያና እሷ ልትሄድ ቆመው እያወሩ ነው።ውጪው ብርድ ስለነበረ፤ ጃሉድ ዝናቡን እያየ "ብርድ ብርድ አለኝ ባክሽ" እያለ እዛው ግጥም ደርሶ ያቀነቅናል።በሰማችው የተመሰጠችው ሲቲያና ስልኳን አውጥታ ቀዳችው።ሙዚቃውን ሰምታ ስትጨርስ ለጃሉድ እኔ ልሄድ ነው፤ ግን ይሄንን ቆንጆ ሙዚቃ አድርጌው ትሰማዋለህ ብላው ሄደች።እንዳለችውም ብርሀኑ ሞገስ የሚባል ሰው፤ ከዛው ሀሳብ ሳይርቅ ግጥም ጨመረበት። ካሙዙ ቅንብሩን ሠራላትና በአልበሟ ላይ የተካተተ ቆንጆ ሥራ ሆነ።የአልበሟ መጠሪያ ለሆነው "ማንነቴን" እና "ዘራፍ ስል" ለተሰኙት ለስለስ ያሉ ሁለት ሙዚቃዎቿ የቪዲዮ ክሊፕ ተሠርቶላቸዋል።የአልበሟ መጠናቀቅን ተከትሎ መኖሪያዋን፤ የትዳር አጋሯ ወደሚገኝበት አሜሪካን ሀገር ቀይራለች።መኖሪያዋ ከሆነው አሜሪካ ተመልሳ፤ የአልበሟን ምርቃት እንዲሁም ኮንሰርት በሀገሯ ስታቀርብ ለመመልከት በመመኘት አበቃን።



# ዓለም አቀፍ

## በጆርጅ ፍሎይድ ግድያ የተፈረደበት ፖሊስ እስር ቤት ውስጥ በስለት ተወጋ

በመላው ዓለም በተለይም በአሜሪካ ከባድ ተቃውሞን ያስከተለውን አፍሪካ አሜሪካዊውን ጆርጅ ፍሎይድን በመግደል ጥፋተኛ የተባለውና 40 ዓመት የተፈረደበት የቀድሞ የፖሊስ አባል እስር ቤት ውስጥ በጩቤ ተወጋ። የሚያኒያ ፖሊስ ግዛት የፖሊሰ መኮንን የነበረው ዴሪክ ሾቪን በግድያው ምክንያት ታስሮ በሚገኝበት የአሪዞና እስር ቤት ውስጥ ጥቃት እንደተፈጸመበት የአሜሪካ መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል።

ምንጮች ለአሶሺየትድ ፕሬስ እንደተናገሩት የ47 ዓመቱ ሾቪን በሌላ እስረኛ በተፈጸመበት የስለት ጥቃት ከባድ ጉዳት ደርሶበታል። ኒው ዮርክ ታይምስም ጉዳዩን የሚያውቁ ሁለት ሰዎችን ጠቅሶ እንደዘገበው የቀድሞው የፖሊስ መኮንን እስር ቤት ውስጥ ጥቃት እንደተፈጸመበት አረጋግጧል።

ዴሪክ ሾቪን ፖሊስ በሚፈጽመው የጭካኔ ድርጊት እና ዘረኝነትን በመቃወም በመላው አሜሪካ ለተቀሰቀሱት መጠነ ሰፊ ተቃውሞዎች ምክንያት ከሆነው የጥቁር አሜሪካዊ ጆርጅ ፍሎይድ ሞት ጋር በተያያዘ የረጅም ዓመታት እስር ተፈርዶበታል። የአሜሪካ የእስር ቤቶች አስተዳደር ቢሮ ባወጣው መግለጫ በቱክሰን ከተማ ውስጥ በሚገኝ የፌደራል መንግሥቱ እስር ቤት ውስጥ አንድ እስረኛ ዓርብ ምሽት በስለት መወጋቱን አረጋግጧል።

ቢሮው ጨምሮም የእስር ቤቱ ሠራተኞች ክስተቱን በመቆጣጠር ጉዳት የደረሰበትን እስረኛ ሕይወት ለመታደግ "የነፍስ አድን ተግባራትን" በመፈጸም ወደ ሆስፒታል መወሰዱን አመልክቷል። ነገር ግን መግለጫው ጉዳት የደረሰበት እስረኛን ማንነት ከመግለጽ ተቆጥቧል። ዴሪክ ሾቪን ከጥቃቱ በሕይወት የተረፈ ሲሆን፣ ከእሱ ውጪ ሌላ ጉዳት የደረሰበት ሰው እንደሌለም ተገልጿል።



የቀደሞው የፖሊስ መኮንን ዴሪክ ሾቪን

ጥቃቱ የተፈጸመው ዴሪክ ሾቪን ከጆርጅ ፍሎይድ ግድያ ጋር በተያያዘ ጉዳዩ ፍትሃዊ በመሆኑ መንገድ አልታየልኝም በሚል ያቀረበውን ቅሬታ የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውድቅ ካደረገበት ከቀናት በኋላ ነው። ጥቁር አሜሪካዊው ጆርጅ ፍሎይድ ከሦስት ዓመት በፊት ለሕልፈት የበቃው ነጩ የፖሊስ መኮንን ዴሪክ ሾቪን መሬት ላይ አስተኝቶ አንገቱ ላይ በጉልበቱ በመርገጥ ከዘጠኝ ደቂቃዎች በላይ ከያዘው በኋላ ነበር።

ይህንን ክስተት በአካባቢው የነበረች አንዲት ወጣት በስልኳ ካሜራ ቀርጻ ካሰራጨችው በኋላ ፖሊሶች በሚፈጽሙት ዘር ተኮር በደል ላይ ከአሜሪካ ባሻገር በመላው ዓለም ቁጣ እና ተከታታይ የተቃውሞ ሰልፎች ተካሂደዋል። በዚህ ድርጊት ለእስር የተዳረገው ሾቪን ከፍሎይድ ግድያ ጋር በተያያዘ በቀረቡበት ክሶች የ22 ዓመት እስር የተፈረደበት ሲሆን፣ በማስከተል ደግሞ የሚቹን መብት በመጣስ ተጨማሪ የ20 ዓመት እስር ተበይኖበታል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።



## ቻይና ለ6 ሀገራት ከቪዛ ነጻ ጉዞ ፈቀደች

ቻይና ለስድስት ሀገራት ከቪዛ ነጻ ጉዞ መፍቀዷን አስታወቀች።ቻይና ለአንድ ዓመት ያለቪዛ ወደ ሀገሯ እንዲገቡ የፈቀደችው ለፈረንሳይ፣ ለጀርመን፣ ለጣሊያን፣ ለኔዘርላንድስ፣ ለስፔን እና ለማሌዥያ ዜጎች መሆኑን የቻይና ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቋል።

በፈረንጆቹ ከመስከረም 30 ቀን 2024 ጀምሮ ፓስፖርት ያላቸው የእነዚህ ሀገራት ተራ ዜጎች ለጉብኝት ወይም ለስራ ወደ ቻይና ተጉዘው ለ15 ቀናት ያህል መቆየት ይችላሉ ተብሏል።የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩ ቃል አቀባይ ማኦ ኒንግ እንደገለጹት፤ቻይና ይህን ርምጃ የወሰደችው የቻይናን ከፍተኛ ጥራት ያለውን እድገት ለማስተዋወቅ ነው።በአሁኑ ወቅት በርካታ ተጓዦች ቻይናን ለማየት ቪዛ ይፈልጋሉ።

ወደ ቻይና ለስራ፣ለቤተሰብ ጥየቃ እና ለጉብኝት ቻይና ሲገቡ የነበሩት የሲንጋፖር እና የብሩናይ ዜጎች ያለቪዛ የመግባት መብት ሳይፈቀድላቸው ቀርቷል።ቻይና ወደ ሀገሯ በሚገቡ ዜጎች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ የጀመረችው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽን ከተከሰተ በኋላ እንደነበር ይታወሳል።

ቻይና ላለፉት ሶስት ዓመታት በርካታ ምርመራዎችን በማድረግ፣ መንገድ በመዝጋት እና ጥብቅ የጉዞ እገዳ በማድረግ ኮሮናን ለመከላከል ከዓለም ጥብቅ የሚባሉ እርምጃዎችን መውሰዷ ይታወሳል።ኮሮና ከመከሰቱ ቀደም ብሎ በ10 ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ቻይናን ይጎበኙ እንደነበር ታውቋል።

**የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ**

1. የንግድ ምልክት ባለቤት ስም፡ ኤች ጄ ሄንዝ ፉድስ ኬ ሊሚትድ (H.J. HEINZ FOODS UK LIMITED) አድራሻ፡ South Building, Hayes Park, Hayes, Middlesex UB4 8AL, United Kingdom
2. የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/1348/2013
3. ንግድ ምልክት::



4. ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በ8/07/2006ዓ.ም በVol-LXXIII No. 188 አዲስ ዘመን ላይ በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ነው::
5. የንግድ ምልክቱ እ.ኤ.አ ከ24/10/2020 እስከ 24/10/2027 እ.ኤ.አ ታድሷል:: በመሆኑም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፈቃድ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል::

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN Vol LXXXIII No 076 16/3/2016 (26/11/2023)

**የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ**

1. የንግድ ምልክት ባለቤት ስም፡ ኤጅዌል ፐርሰናል ኬር ብራንድስ ኤልኤልሲ (EDGEWELL PERSONAL CARE BRANDS, LLC) አድራሻ፡ 6 Research Drive, Shelton, Connecticut 06484, United states of America
2. የማመልከቻ ቁጥር፡ FTM/2143/2014
3. የንግድ ምልክት::

EXACTA

4. ባለቤቱ የንግድ ምልክቱን የሚጠቀምበት በ22/2/2005 ዓ.ም በVol-LXVII No.52 አዲስ ዘመን ላይ በወጣው ማስታወቂያ ላይ ለተዘረዘሩት ዕቃዎችና አልግሎቶች ነው::
5.የንግድ ምልክቱ እ.ኤ.አ ከ08/09/2021 እስከ 08/09/2028 እ.ኤ.አ ታድሷል በመሆም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፈቃድ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል::

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

ADDIS ZEMEN Vol LXXXIII No 076 16/3/2016 (26/11/2023)

**የጨረታ ማስታወቂያ**

**የሀገር ውስጥ የጨረታ ቁጥር ሙሲፋ/43/2016**

በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ለሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ አገልግሎት የሚውል Split Type Air Conditioner በጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል:: ስለዚህ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ ተጫራቾች የማይመለስ ብር 115.00 ከነቫቱ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን አዲስ አበባ በቅሎ ቤት አካባቢ ጋራድ ህንጻ ቢሮ ቁጥር 432-3-8 ከሚገኘው የግዢ መምሪያ ቢሮ እየቀረቡ መግዛት ይችላሉ:: ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) በባንክ በተረጋገጠ ቼክ CPO ወይም በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ባንክ ጋራንቲ ከቴክኒክ ዶክመንቶቹ ጋር በማያያዝ ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ታህሳስ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 3:30 ሰዓት ድረስ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ የጨረታ ሰነዳቸውን አዲስ አበባ በሚገኘው በግዢ መምሪያ በተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል:: ጨረታው በዕለቱ ታህሳስ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት በግዢ መምሪያ ይከፈታል::

ፋብሪካው ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

ስልክ ቁጥር፡- 011-442-02-16

ፋክስ፡– 011-442-06-88

አዲስ አበባ

**በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን**

**ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ**

**Invitation for Bid**

**Title: Procurement of Printing Agenda 2017 E.C**

**Procurement Reference number: Re Bid-SCO/NCB/G/02/2016 E.C**

1. The Supreme Court of Oromia has a mandate to Procure the below mentioned goods who has funds within the government budget to be used.
2. The Supreme Court Of Oromia invites sealed bids from eligible bidders for the supply and delivery of:

| Lot | Item | Description | Unit of | Quantity |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 1.1 | Court Agenda 2017 E.C | Pcs | 4,000 |
| | 1.2 | Administrative Agenda 2017 E.C | pcs | 200 |

3. Bidding will be conducted through National Competitive Bidding (NCB) procedures Contained in the Public Procurement Proclamation of the Federal and Regional Government of Oromia and are open to all eligible bidders.
4. Interested eligible bidders may obtain further information from Supreme Court of Oromia at the address given below from Monday to Friday from 09:00 a.m. to 12:00 am in the morning and 7:30 p.m. to 10:30 p.m. in the afternoon.
5. A complete set of Bidding Documents in English may be purchased by interested bidders at the address below and upon payment of a non-refundable fee of Ethiopian Birr 200 (two hundred). The method of payment will be Cash on site.
6. Bidders shall submit bid security 2% (two percent) of the total bid price in the form of CPO or unconditional bank guarantee from recognized Bank and valid for 28 days beyond bid validity.
7. Bids must be delivered to the address below at or before December 15, 2023 G.C. at 11:00 a.m. in the morning. Late bids shall be rejected.
8. Bids will be opened in the presence of the bidders /representatives who choose to attend at the address below December 15, 2023 G.C at 11:05 a.m. in the morning.
9. The Supreme Court of Oromia reserves the right to reject any bid and to annul the bidding process and reject all bids at any time prior to contract award, without thereby incurring any liability to bidders.
10. Address of documents issued from, inspected at, and bids delivered at: Supreme Court of Oromia

**Street: Kirkos Sub-city Woreda 05 (Sarbet Oromia Bureau)**

**Floor/Room number: 3rd floor Procurement and Financial Administration**

**Directorate Telephone: 011-123 44 29/31 or 011-123 44 37**

**Town/City: Addis Ababa**

**PO Box: 26110**

**Country: Ethiopia**

**Supreme Court of Oromia**

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# የኢትዮጵያ አየር መንገድ ...

**ከገጽ 3 የዞረ**

ጭቃና አረንቋ ሳይበግረው ሕዝቡ 15 ኪሎ ሜትር አቋርጦ በባዶ እግሩ ወደ ገፈርሳ ይተማል።

ንጉሡ ከነሚኒስትሮቻቸው፣ መኳንንቱና መሳፍንቱ፣ ዲፕሎማቶችና የሃይማኖት አባቶች ሳይቀሩ የታደሙበት ይኼ ክስተት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እጅግ እንግዳ የሆነውን ነገር ይዞ ሊመጣ ነው። ገፈርሳ ላይ በአበባ፣ በዘንባባና በሰንደቅ ዓላማ ያሸበረቁ ድንኳኖች ተዘጋጅተዋል፤ ገፈርሳ እጅግ ተሞሽራለች። ይህ ሁሉ ሽር ጉድ ‹‹በራሪውን የሰይጣን ክንፍ›› ለማየት ነበር። ሕዝቡ በርቀት በሚያያቸው አሞሮች ላይ ሁሉ እጁን እየቀሰረና ዓይኑንም እየሸነቆረ ‹‹በራሪውን ሰይጣን›› ቀድሞ ለማየት አብዝቶ ታገሰ።

ከብዙ ጥበቃና ትዕግሥት በኋላ ግን የሆነ ድምፅ ከርቀት ይሰማ ጀመር። ሕዝቡ በሁሉም አቅጣጫ ያለውን የሰማይ ጥግ ላይ ሁሉ በዓይኑ አማተረ። ወቅቱ ክረምት ነው፤ ሰማዩ ዳምኗል። ምንም የሚታይ ነገር ሳይኖር ድምፅ ብቻ ይመጣል፤ ድምፅ ብቻ ሕዝቡን ይዞራል። ድምፁም በጣም እየቀረበና ይበልጥ እየጮኸ ሲመጣ የሕዝቡ ጉጉት ወደ ድንጋጤና ፍርኃት ተቀየረ። ድንገት ግን ‹‹በራሪው የሰይጣን ክንፍ›› ድርብርቦሹን ደመና ቀዶ ወጣ። ሰይጣኑ አናቱ ላይ እንዳያርፍበት ሕዝቡ በየአቅጣጫው ይፈረጥጥ ጀመር። ድንጋጤና ግርምት፣ ፍርኃትና ጉጉት የናጠው የሕዝብ ትርምስ። ገፈርሳ ግራ ገባት።

‹‹በራሪው የሰይጣን ክንፍ›› ግን በሕዝብ ግርግር ሳይደናገጥ ሕዝቡን እንደ ታቦት ዞሮ ድንገት ድንኳኖቹ ፊት ለፊት ዠርገግ ብሎ አረፈ። ትርምሱ ቆመ፣ ድንጋጤው ወደ ፈንጠዝያ ተቀየረ። ገፈርሳን ዕልልታ፣ ፉጨትና ጩኸት ዋጣት! ሕዝቡ ካፒቴኑን ተሸክመው ተቀባበሉት፤ ገፈርሳ በፉከራና በሽለላ ተናጠች። እዚያ ቦታ ላይ ሆኖ ያንን ፈንጠዝያ፣ ያንን ጩኸት የማይጋራ ሊኖር አይችልም።

ንጉሥ ተፈሪም ዘለው ከድንኳናቸው ወጡ፤ እንባ እየተናነቃቸውም ተስፈንጥረው ካፒቴኑ ላይ ተጠመጠሙበት። ሕዝቡ ከንጉሣቸው ጋር በአንድ ላይ ሲቃ ውስጥ የገቡበት ክስተት ነው የመጀመሪያዋ ፓቴዝ አውሮፕላን ወደ አገራችን መምጣት። በመሆኑም የኢትዮጵያ የአቪዬሽን ታሪክ የሚጀምረው ሕዝቡንና መሪውን በአንድ የታሪክ ሲቃ ላይ በመግመድ ነው።

ይኼ የሕዝቡ ሲቃ ግን እንዲሁ እንግዳ በሆነ ክስተት ብቻ የተፈጠረ አይደለም። ይልቅስ ታሪክ ላይ የተመረኮዘ ገፊ ኃይል አለው እንጂ። የኢትዮጵያን ‹‹የቀድሞ ማዕረጓንና ኃይሏን›› የመመለስ እልህ። ንጉሥ ተፈሪም በዚያው ክስተት ላይ ያሰሙት ንግግርም ይኼንኑ የሚያረጋግጥ ነው። ‹‹ኢትዮጵያ...›› አሉ ንጉሡ፣ ‹‹ኢትዮጵያ በጥንት ሥልጣኔዋ ዘመን ከኢየሩሳሌምና ከዓረብ፣ ከሕንድም መንግሥታት ጋር በንግድና በፖለቲካ ትገናኝ ነበር።

አሁንም ያንን ማዕረጓንና ኃይሏን ለመመለስ፣ እንዲሁም የአገር ውስጥ ጉዳያችንን በፍጥነት ለመፈጸም እንዲረዳን ይኼንን የአየር ባቡር አስመጣን።›› ይኼንን የንጉሡን ንግግር ስናሳጥረው የአገራችን የአቪዬሽን ታሪክ ገና ከመነሾው ሁለት ተልዕኮዎችን አንግቦ የተነሳ ነው። ብሔራዊ ኩራትን

**‹‹በራሪው የሰይጣን ክንፍ‹‹ ግን በሕዝብ ግርግር ሳይደናገጥ ሕዝቡን እንደ ታቦት ዞሮ ድንገት ድንኳኖቹ ፊት ለፊት ዠርገግ ብሎ አረፈ። ትርምሱ ቆመ፣ ድንጋጤው ወደ ፈንጠዝያ ተቀየረ። ገፈርሳን ዕልልታ፣ ፉጨትና ጩኸት ዋጣት! ሕዝቡ ካፒቴኑን ተሸክመው ተቀባበሉት፤ ገፈርሳ በፉከራና በሽለላ ተናጠች። እዚያ ቦታ ላይ ሆኖ ያንን ፈንጠዝያ፣ ያንን ጩኸት የማይጋራ ሲኖር አይችልም**

መመለስና ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን መቀዳጀት።

‹‹ኢኮኖሚያዊ ጥቅም›› የሚለውን ተልዕኮ የተቀበለው ከራሱ ከአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ባህሪ ሲሆን፣ ‹‹ብሔራዊ ኩራትን መመለስ›› የሚለውን ተልዕኮ የተቀበለው ደግሞ ከሕዝቦቿ ‹‹ታሪካዊ ሲቃ›› ነው። በዚህ አገራዊ ርዕይ አማካይነት አቪዬሽን የትውልዱን ቁጭት ይዞ የአገሪቱ ታሪክና ርዕይ ተጋሪ ሆኗል። በዚህ ተልዕኮም የኢትዮጵያ አቪዬሽን ከአገራችን ታሪክ ጋር ብዙ ውጣ ውረዶችን አብሮ አሳልፏል።

በመሆኑም የኢትዮጵያን የአቪዬሽን ታሪክ ከአገሪቱ ታሪክ ነጥለን ልንመለከተው አንችልም። የመጀመሪያዋ አውሮፕላን ወደ ኢትዮጵያ የገባችበትን ዘመን በአገሪቱ የታሪክ ሒደት ውስጥ ከተን ስንመለከተው፣ ከዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ጀምሮ ኢትዮጵያን የማዘመንና የቀድሞ ክብሯን ለመመለስ ሲደረጉ ከነበሩ ጥረቶች መካከል አንዱ ሆኖ እናገኘዋለን።

ከ1921 እስከ 1928 ዓ.ም. የፋሽስት ወረራ ጊዜ ድረስ የነበሩት ሰባት ዓመታት የኢትዮጵያ የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ጠንካራ መሠረት የተጣለበት ወቅት ነበር። አውሮፕላን ከማብረር እስከ አውሮፕላን መሥራት፣ ከበረራ ትምህርት ቤት እስከ አውሮፕላን መጠገኛ ጋራዥ (ሀንጋር)፣ ከኢትዮጵያውያን አውሮፕላን ጠጋኞች እስከ ሴት አብራሪዎችን ማፍራት የተቻለበት ወቅት ነበር። የፋሽስት ወረራ ግን ሁሉን ነገር አወደመው፣ ሁሉን በዜሮ አባዛው።

የኢትዮጵያ የአቪዬሽን ታሪክ ከአገራችን ታሪክ ጋር ብዙ ውጣ ውረዶችን አብሮ አሳልፏል። በፋሽስቶች በተወረርንበት ወቅት እሱም አብሮ ተወሯል። በድል አድራጊነት በዓለም መድረክ ላይ ቀና ባልንበት ጊዜም፣ እሱም ከእኛ ጋር ቀና ብሏል። አገራችን ከፋሽስት ወረራ በ1933 ዓ.ም. ነፃ በወጣች ማግሥት የአገራችን የነፃነት ብሥራት ሆኖ የተቋቋመው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ነው። አየር መንገዱ በዚህ ታሪካዊ ወቅት መቋቋሙ ከኋላ የአገሪቱን ቁጭት፣ ከፊት ደግሞ የሕዝቦቿን ራዕይ ተሸክሞ የሚበር አየር መንገድ እንዲሆን አድርጎታል።

ምሥጋና ለጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ይሁንና በኢትዮጵያ መንግሥትና በአሜሪካው ትራንስ ወርልድ ኤርላይንስ (TWA) ኩባንያ መካከል በተደረሰ ስምምነት መስከረም 1 ቀን 1938 ዓ.ም. በ2.5 ሚሊዮን ብር የኢትዮጵያ አየር መንገድ በቦርድ ተቋቋመ። የመጀመሪያ ዓለም አቀፍ በረራውንም መጋቢት 30 ቀን 1938 ዓ.ም. በአስመራ በኩል በማድረግ ወደ ካይሮ አደረገ።

ከዚህ በኋላ አየር መንገዱ አገሪቱ የምትገኝበትን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታና የጥንታዊ ቅርስ ባለቤትነት ዕድሎችን እየተጠቀመ በፍጥነት ማደግ ጀመረ። ከተቋቋመ ገና በአራተኛ ዓመቱም ዓለም አቀፍ በረራዎቹን ከካይሮ በተጨማሪ ወደ ጅቡቲ፣ ኤደን፣ ጅዳ፣ ናይሮቢ፣ ፖርት ሱዳን፣ ካርቱም፣ ቦንቤና ካራቺ አስፍቷል።

በኢትዮጵያ የአቪዬሽን ታሪክ ውስጥ አጠቃላይ ኢንዱስትሪውን ሥር ነቀል ወደ ሆነ የላቀ ደረጃ የወሰዱ ሁለት አብዮቶች ተከስተዋል። ሁለቱም አብዮቶች ታዲያ የተከሰቱት በኢትዮጵያ አየር መንገድ የዕድገት ግፊት የተነሳ ነው። የመጀመሪያው አብዮት የመጣው የኢትዮጵያ አየር መንገድ በ1952 ዓ.ም. የቦይንግ ጄት አውሮፕላኖችን ለመግዛት በመወሰኑ ነው።

ይህ ውሳኔ አብዮት ያስከተለበት ምክንያት ደግሞ በወቅቱ የነበረውና በጣሊያን የተሠራው የልደታው አየር ማረፊያ፣ አዲስ የሚገዙትን ጄት አውሮፕላኖች የማስተናገድ ብቃት የሌለው መሆኑ ነው። በመሆኑም ውሳኔው ሌላ አዲስ ዘመናዊ ኤርፖርት ቦሌ ላይ እንዲሠራ ከማድረጉም በተጨማሪ የቅኝት (Air Navigation) እና የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ መሣሪያዎችም ከጊዜው ጋር እንዲዘምኑ ምክንያት ሆኗል።

ከአዲሱ ኤርፖርት ግንባታ ጎን ለጎንም አየር መንገዱን ኢትዮጵያዊ የማድረጉ ከፍተኛ ጥረትም የሚዘነጋ አይደለም። የአየር መንገዱን ቁልፍ የሥራ ሒደቶችን (የበረራ፣ የጥገና፣ የሽያጭና የአስተዳደር ሥራዎችን) ከአሜሪካውያን ተረክቦ በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች የመተካቱ ጥረት እየተሳካ ሄዶ፣ በ1963 ዓ.ም. ኮሎኔል ስምረት መድህኔን የመጀመሪያው የአየር መንገዱ ኢትዮጵያዊ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አድርጎ በመሾም ትልቅ ዕመርታ አስመዘገበ።

ሁለተኛው አብዮት ደግሞ ርዕይ 2025 (እ.ኤ.አ.) ነው። ይህ ርዕይ ልክ እንደ 1952 ዓ.ም. ውሳኔ ሁሉ በአዲስ አበባ ኤርፖርትና በአየር ትራፊክ ቁጥጥሩ ላይ ሥር ነቀል ለውጥ እንዲመጣ ያስገደደ ክስተት ብቻ ሳይሆን፣ የአየር መንገዱንም የውስጥ አደረጃጀት ከመሠረቱ እየቀየረ ያለ ውሳኔ ነው። እ.ኤ.አ በ2010 የተቀረፀው ይህ የ15 ዓመት የዕድገት መርሐ ግብር አየር መንገዱን ወደ ሰባት የተለያዩ የትርፍ ማዕከልነት በማዋቀር ወደ ግዙፍ የአቪዬሽን ግሩፕ ኮርፖሬትነት እያሳደገው ይገኛል።

በዚህም አየር መንገዱን እ.ኤ.አ. በ2025 በ112 አውሮፕላኖች 18 ሚሊዮን መንገደኞችንና 710,000 ቶን ጭነቶችን ወደ 92 ዓለም አቀፍ መዳረሻዎች በማጓጓዝ በዓመት አንድ ቢሊዮን ዶላር ትርፍ ላይ ለመድረስ አልሟል። በእርግጥ አየር መንገዱ በአሁኑ ወቅት የዓለም አቀፍ መዳረሻዎችን ብዛት 92 በማድረስ ከዕቅዱ አሥር ዓመት ቀድሞ ማሳካት ችሏል።

ይህ የአየር መንገዱ ርዕይ የአዲስ አበባ ዓለም አቀፍ ኤርፖርትን በሁለት ዙር፣ በ2004 ዓ.ም. በ1.1 ቢሊየን ብር እና በአሁኑ ወቅት ደግሞ በአምስት ቢሊዮን ብር፣ ግዙፍ የማስፋፊያ ፕሮጀክቶች ውስጥ እንዲገባ ከማድረጉም ባሻገር፣ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት በአዲስ አበባ አቅራቢያ ሌላ ግዙፍ የኤርፖርት ከተማ የመገንባት ውሳኔ ላይ እንዲደርስ ምክንያት ሆኗል።

በአየር ትራፊክ ቁጥጥሩ ላይም ከፕሮሲጀራል ቁጥጥር እጅግ ዘመናዊ ወደሆነው የራዳር የአየር ትራፊክ ቁጥጥሩ እንዲቀየር ምክንያት ሆኗል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ እንደ ቦይንግ B787 እና ኤርባስ A350 ያሉ ዘመናዊ አውሮፕላኖች ባለቤት የመሆን ጥረቱም ሆነ፣ በሌሎች አየር መንገዶች ላይም እያደረገ ያለው ኢንቨስትመንትም የዚሁ ርዕይ 2025 አካል ነው።

ሻሎም ! አሜን።

# ስፖርት





## የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የማራቶን ሪሌ አሸናፊ ሆነ

ብርሃን ፈይሳ

ኢትዮጵያን በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች ወክለው ውጤታማ የሆኑ በርካታ አትሌቶችን በማፍራት ተጠቃሽ ከሆኑ ክልሎች መካከል ትግራይ አንዱ ነው። ክልሉ በነበረው ጦርነት ለዓመታት ከስፖርት እንቅስቃሴ ርቆ የቆየ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደ መደበኛ እንቅስቃሴዎች እየተመለሰ ይገኛል። የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንም በክልሉ 19ኛውን የማራቶን ሪሌ ውድድርን ትናንት በመቀሌ ከተማ በማካሄድ ስፖርቱን የማነቃቃት ሥራ አከናውኗል።

አትሌቶች 42 ኪሎ ሜትሮችን ተከፋፍለው ዱላ በመቀባበል የሚያደርጉት  የሪሌ ውድድርም መነሻና መድረሻውን በሰማዕታት ሐውልት በማድረግ ተካሂዷል። በውድድሩም ላይ የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፣ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት ጄነራል ጻድቃን ገብረትንሳይ፣ የክልሉ ስፖርት ኮሚሽነር ተክላይ ፈቃዱ፣ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ምክትል ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ፣ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት እንዲሁም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

ጠንካራ ፉክክር በታየበት ውድድር ላይም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አትሌቲክስ ቡድን አሸናፊ በመሆን የወርቅ ሜዳሊያ፣ የዋንጫ እንዲሁም የገንዘብ ሽልማቱን ወስዷል። የኢትዮ ኤሌክትሪክ እና የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ክለብ ደግሞ ሁለተኛና ሦስተኛ በመሆን አጠናቀዋል። በውድድሩም ላይ አምስት ክልሎችና ዘጠኝ ክለቦች 84 አትሌቶችን አሳትፈዋል። በውድድሩ በርካታ ታዋቂ አትሌቶች የተሳታፉ ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል አትሌት ሰለሞን ባረጋ፣ ሰንበሬ ተፈሪ፣ ጽጌ ገብረሰላማ እና ደራ ዲዳ ጥቂቶቹ ናቸው።

ውድድሩን በሚመለከት የአሸናፊው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አትሌቲክስ ቡድን አባል የሆነችው አትሌት ካሳነሽ አየነው ስትናገር፣ ውድድሩ  ፉክክር የታየበት ቢሆንም በጠንካራ የቡድን ሥራ አሸናፊ ሊሆኑ መቻላቸውን ገልጻለች። ከ5 ኪሎ ሜትር እስከ ግማሽ ማራቶን ባሉት ርቀቶች በበርካታ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ የተሳተፈችው አትሌቷ መሰል ውድድሮች የአትሌቶችን አቅም ለማየት የሚያግዝ መሆኑን ተናግራለች። በተለይም በዓለም አቀፍ ደረጃ የመም ውድድሮች እየጠፉ በመሆናቸው እንዲሁም በኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ የመም ችግር ያለ በመሆኑ መሰል ውድድር ጠቀሜታው ከፍተኛ በመሆኑ ሊስፋፉ እንደሚገባ አመላክታለች።

በውድድሩ ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ ያጠናቀቀውና ያገኘውን የገንዘብ ሽልማት በክልሉ ለተፈናቀሉ ወገኖች ድጋፍ እንዲውል ያደረገው የኢትዮ ኤሌክትሪክ ስፖርት ክለብ ሲሆን፣  ክለቡን በመወከል ከተወዳደሩት አትሌቶች መካከል አንዱ የሆነው ጸጋዬ ኪዳን፤ በሪጋ በተካሄደው የዓለም የጎዳና ላይ ቻምፒዮና 21ኪሎ ሜትር ውድድር ኢትዮጵያን ወክሏል። በዚህ ውድድር ላይም ጠንካራ ውድድር በማድረግ የብር ሜዳሊያ በማግኘታቸው መደሰቱን ገልጿል። የጎዳና ውድድሮች በየጊዜው በሀገር ውስጥ መደረጋቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚካፈሉባቸው ውድድሮች እንደሚጠቅሟቸውም ይጠቅሳል።

የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፤ ክልሉ በርካታ ስፖርተኞችን ለሀገር ያፈራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከሰላም ስምምነቱ በኋላ ወጣቱን ወደ ስፖርት ለመመለስ እንዲሁም ለመልሶ ግንባታ የሚወጣውን ሚና በተግባር እያሳየ መሆኑን ገልጸዋል። በስፖርት አማካኝነት አትሌቶች እንዲገናኙ ያደረገው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ምስጋና ይገባዋል ሲሉም ተናግረዋል። ሌሎች የስፖርት ማኅበራትም በተመሳሳይ ለሰላም ግንባታው የበኩላቸውን ሚና ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል።




የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወርቅ ሜዳሊያና የዋንጫ ተሸላሚ ሆኗል፣

በውድድሩ ላይ በመገኘት ለአሸናፊዎች የዋንጫ ሽልማት ያበረከቱት የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት ጄኔራል ጻድቃን በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ይህንን ውድድር በመቀሌ በማካሄዱ ምስጋናቸውን አቅርበዋል። ፌዴሬሽኑ በጦርነቱ ወቅት የትግራይ ክልል አትሌቶችን በመደገፍ ውጤታማ እንዲሆኑ አስተዋጽኦ ማበርከቱንም አስታውሰዋል። «ስፖርት የሰላምና የወዳጅነት መሣሪያ በመሆኑ ወጣቶችን ያንጻል። በመሆኑም ሌሎች የስፖርት ማኅበራትም ወደ ክልሉ በመምጣት ጉዳት የደረሰባቸውን የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በመገንባትና የፈራረሱ የስፖርት አደረጃጀቶችን በማስተካከል ሊያግዙ ይገባል» ሲሉም ጥሪ አቅርበዋል።

የክልሉ ስፖርት ኮሚሽነር አቶ ተክላይ ፈቃዱም ይህ ውድድር እንዲሁም የፌዴሬሽኑ ጠቅላላ ጉባኤ በመቀሌ እንዲደረግ ክልሉ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት በማግኘቱ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን አመስግነዋል። በቀጣይም ሌሎች ጉባኤዎችን በማድረግ መነጋገርና መወያየት እንደሚያስፈልግና እንደክልል ወደነበረበት የስፖርት አቋም ለመመለስ እገዛ እንደሚሹም ጠቁመዋል።


# የግልጽ ጨረታ ግዥ ማስታወቂያ ቁጥር 002/2016

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትሕ ቢሮ በ2016 በጀት ዓመት በ2ኛ ዙር ግልጽ ጨረታ ለቢሮው ዐቃቢያነ ህጎች አገልግሎት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሥራ ልብስ ግዥዎችን በጨረታ አወዳድሮ ግዥ መፈፀም ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ ልብስ ዓይነት | መስኪያ | ልዩ መግለጫ |
|---|---|---|---|
| 1 | የወንድ ሙሉ ልብስ | በቁጥር | ሬዲሜድ ሙሉ ከሱፍ ጨርቅ የተሰፋና ገበር ያለው ስታንዳር ዱን የጠበቀ (ለዓቃቢያነ ሕግ) |
| 2 | የወንድ ሸሚዝ | በቁጥር | ሙሉ በሙሉ ስታንዳርዱን የጠበቀ (ለዓቃቢያነ ሕግ) |
| 3 | የሲት ሙሉ ልብስ (ኮትና ሱሪ ወይም ኮትና ቀሚስ) | በቁጥር | ሬዲሜድ ሙሉ ከሱፍ ጨርቅ የተሰፋና ገበር ያለው(ለዓቃቢያነ ሕግ) |
| 4 | የሴት ሸሚዝ | በቁጥር | ሙሉ በሙሉ ስታንዳርዱን የጠበቀ \|mport standard (ለዓቃቢያነ ሕግ) |
| 5 | የወንድ ከረቫት | በቁጥር | ጥራቱን የጠበቀ Import (ለዓቃቢያነ ሕግ) |
| 6 | የወንድ አጭር ጫማ | በቁጥር | ከንፁህ ቆዳ የተሠራ Import & Export standard (ለዓቃቢያነ ሕግ) |
| 7 | የሴት አጭር ጫማ | በቁጥር | ከንፁህ ቆዳ የተሠራ Import & Export standard (ለዓቃቢያነ ሕግ) |

### በዚህ በጨረታው መወዳደር የምትችሉት፡-

1. ሕጋዊ የታደሰ የንግድ ፈቃዳቸውንና የዘመኑን ግብር የከፈሉበትን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፣
2. የገንዘብ ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባዘጋጀውና አቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ለመመዝገባቸው የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፣
3. ግብር የመከፈል ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን የሚያረጋግጥ በግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን የተሰጠ ማስረጃ፣
4. በመንግሥት ግዥ እንዳይሳተፍ ታግዶ የነበረ ከሆነ የዕገዳ ጊዜውን ያጠናቀቀ፣
5. ውል ለመፈፀም የሚያስችል የህግ ችሎታ ያለው፣
6. ተጫራቹ በጨረታው ለመሳተፍ ብቃት ያለው መሆኑንና ዕቃው በስቶክ ያለው መሆኑን ማስረጃ የሚያቀርብ፣
7. ተጫራቾች የጨረታ ዝርዝር የያዘ ሰነድ ለሚጫረቱበት የማይመለስ ብር 50 (ሀምሳ ብር) በመክፈል ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ለ10/ የሥራ ቀናት ዘወትር በስራ ሰዓት አዲስ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ በግዥ ንብረት ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት 7ኛ ፎቅ ላይ በመገኘት መግዛት ይችላሉ፣
8. ተጫራቾች ናሙና እንዲያቀርቡ የተጠየቁባቸውን ዕቃዎች መጫረቻ ሠነዳቸውን ሲያስገቡ አብረው የሚወዳደሩበትና ናሙና የማስገባት ግዴታ አለባቸው፤
9. ተጫራቾች ለሚጫረቱበት ዕቃ 2% በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ስም ብር 2,000 ማስያዝ ይኖርባቸዋል፤ እንዲሁም አሸናፊው ድርጅት የውል ስምምነት ሲፈርም የውል ማስከበሪያ ካሸነፈበት ዋጋ 10% ያስይዛል::

10 ተጫራቾች በገዙት ሰነድ ላይ ብቻ ዋጋ በመሙላትና ማህተም በማድረግ ፖስታቸውን በማሸግ ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ ቀናት ለዚሁ በተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

11. የቴክኒካል ሠነድ ኦርጅናልና ኮፒ፣ የፋይናንሻል ሠነድ ኦርጅናልና ኮፒ በማለት ለይቶ በተገዛው ሰነድ ላይ ያለምንም ሥርዝ ድልዝ ሞልተው ማቅረብ አለባቸው፣
12. ከአሸናፊው ተጫራጭ ጋር ውል ከመፈረሙ በፊት በጨረታ ሰነዱ ከተገለፀው  አቅርቦት መጠን በላይ መጨመር ወይም መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በአሸናፊው ተጫራች የቀረበው በውድድሩ የተገኘው ዋጋ ሣይቀየር እስከ 25%መጨመር ወይም መቀነስ እንደሚቻል፣
13. ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 10 ቀናት ቆይቶ በ11ኛው ቀን ጠዋት 3፡00 ሰአት ላይ ተዘግቶ በዛው እለት ጥዋት 3፡30 ሰአት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡ ከተጠቀሰው ቀን ዘይግቶ የሚመጣ የጨረታ ሰነድ ዋጋ አይኖረውም፣
14. መስሪያ ቤቱ ለጨረታው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 0115159548 በመደወል መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡**
**አድራሻችን- ሜክሲኮ ፊሊፕስ አጠገብ ወይም ጨለለቅ አልሳም ታወር ፊትለፊት**

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትሕ ቢሮ




# የሕፃናት ቀን - ‹‹በልጅ ዓይን ሁሉም ንጹህ ነው››

እዮሩስ ተስፋዬ

ሰላም ልጆች እንዴት ናችሁ? ትምህርት እንዴት ነው? በሚገባ እያጠናችሁ እንደሆን ተስፋ አደርጋለሁ። ልጆችዬ እንኳን አደረሳችሁ? መቼም የምን በዓል ኖሮ ነው እንኳን አደረሳችሁ የተባልነው? ልትሉ ትችላላችሁ። ለምን መሰላችሁ? የሕፃናት ቀን ባሳለፍነው ሳምንት መከበሩን ምክንያት በማድረግ ነው። ‹‹እንኳን አብሮ አደረሰን።›› የሚል ምላሽ እንደምትሰጡኝ ምንም ጥርጥር የለኝም።

ልጆች የሕፃናት ቀን እንዴት መከበር እንደተጀመረ ጥቂት እናስታውሳችሁ አይደል? እኤአ በ1959 የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የሕፃናት መብቶች መግለጫ ያፀደቀበት ቀን ኅዳር 20 ነበር። በተጨማሪም በ1989 የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ያፀደቀበት ቀን እንደሆነ ይታወቃል። በዚህም ምክንያት የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ከፀደቀበት ቀን እና የሕፃናት መብቶች መግለጫ የፀደቀበትን ቀን ለማስታወስ እ.ኤ.አ. ከ1990 ጀምሮ የዓለም የሕፃናት ቀን ኅዳር 11 ይከበራል ማለት ነው።

ታዲያ ልጆችዬ ይህንን ምክንያት በማድረግ በየዓመቱ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው የሕፃናትን መብት፣ ደህንነትን እና ክብካቤን እንዲጎለብት የሚያላክቱ መልዕክቶችን እንዲሁም የተለያዩ ዝግጅቶችን በመቅረጽ መንግሥታዊ በመሆኑ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ይከበራል። ዘንድሮም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ35ተኛ ጊዜ በሀገራችን ደግሞ ለ18ኛ ጊዜ ተከብሯል።

ስለዚህም የሕፃናትን ቀን በማስመልከት ከተደረጉት ዝግጅቶች መካከል ቅዳሜ ኅዳር 08 ቀን 2016 ዓ.ም በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ‹‹በልጅ ዓይን ሁሉም ንጹህ ነው›› በሚል መሪ ሃሳብ በድምቀት የተከበረው ፌስቲቫል አንዱ ነው። በዚህ ፌስቲቫል ላይ የሕፃናት መጽሐፍት ኤግዚቢሽን፣



እ.ኤ.አ. ከ1990 ጀምሮ የዓለም የሕፃናት ቀን ኅዳር 11 ይከበራል፣

የሕፃናት ማርሽ ባንድ፣ የሰርከስ ትርኢት፣ ግጥም፣ ሙዚቃ እና ሌሎች ዝግጅቶችም ቀርበዋል።

በሰም እና ወርቅ ሚዲያ እና ኢንተርቴመንት በተዘጋጀው በዚህ ፌስቲቫል ላይ መስማት ለተሳናቸው ታዳሚዎችም በምልክት ቋንቋ መልዕክቶች ሲተላለፉ ነበር። እንዲሁም የሜሪ ጆይ የልማት አቀፍ ሕፃናት ማኅበር አባላት መዝሙሮችን ያቀረቡ ሲሆን፡-

ይብቃ ይብቃ የጎዳና ሕይወት፤

ይበቃ ይቁም የሕፃናት ጥቃት።

የሚል የሕፃናት መዝሙር በማቅረብ የጎዳና ሕይወት አስከፊ መሆኑን ፤ ትኩረት ጎዳና ላይ ላሉ ልጆች ማድረግ እንደሚገባም በመልዕክታቸው አስተላልፈዋል። በተጨማሪም ልጆች ሀገራቸውን እንዴት እንደሚወዱ እና ሀገራቸውን በሚገባ በግጥም መልክ አቅርበዋል።

የፌስቲቫሉ አዘጋጅ ጌታቸው ዓለሙ ስለፌስቲቫሉ ዓላማ ሲናገር በምርምር፣ በሀገር በቀል ሥራዎች፣ በቴክኖሎጂ፣ ሥነ ፈለክ እንዲሁም በትምህርት ጎበዝ የሆኑ ተማሪዎችን በመሸለም እና በማበረታታት ከዚህ ከፍ ሲልም ተስፋ ሊሰጥ የሚችል ትውልድ ለመቅረጽ እና ሌሎችንም ለማነቃቃት ትኩረት ያደረገ ነው።

በፌስቲቫሉ ላይ የግጥም ሥራዎቻቸውን ካቀረቡት መካከል ቃለአብ ሸዋፈራሁ አንዱ ሲሆን፤ የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ነው። በዓሉን ለማክበር ስለተደረገው ዝግጅት እንዲሁም ግጥሙን ለታዳሚዎች ለማቅረብ ዕድሉን በማግኘቱ ምስጋናውን አቅርቧል። ሌላው በፌስቲቫሉ ላይ ከታደሙት ሕፃናት መካከል እህትማማቾቹ ኤፍራታ ዓለሙ እና ዮስቲና ዓለሙ ናቸው። እነርሱ እንደሚሉት የሕፃናት ቀን በዚህ መልኩ በመከበሩ ደስታቸውን ገልጸዋል። በዕለቱ ሽልማት እንደተሰጣቸው ልጆች ለመሸለምም በርትተው እንደሚያጠኑ ተናግረዋል።

በዚህ ፌስቲቫል ወላጆችም ተገኝተዋል። የፌስቲቫሉ ታዳሚ ወይዘሮ ቅድስት መኮንን እንዳሉት ፌስቲቫሉ ለልጆች በጣም ደስ የሚል እንደሆነ ነው የገለጹት። እንዲህ ዓይነቱ ፌስቲቫል ልጆችን ከማጫወት ባሻገር ከወላጆቻቸው ጋር በጋራ እንዲያሳልፉ ዕድል የሚሰጥ መሆን ገልጸዋል። በተጨማሪም ለሽልማት የበቁትን እንዲሁም የተለያዩ ሥራዎችን ሲያቀርቡ የነበሩ ልጆችን በመመልከት ልጆች የራሳቸውን ፍላጎት እንዲያጤኑ የሚያደርግ መሆኑን አስታውቀዋል።

ልጆችዬ በዚህ ፌስቲቫል ላይ ከተገኙት መካከል ዶክተር አሉላ ፓንክረስት፣ የሙዚቃ ባለሙያ የክብር ዶክተር ዳዊት ይፍሩ፣ ሰዓሊ ጋሽ አክሊሉ መንግሥቱ እና የሜሪጆይ ኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ማኅበር መሥራች ሲስተር ዘቢደር ዘውዴ የተገኙ ሲሆን፤ ልጆች በጥሩ መንገድ መቀረጽ እንዳለባቸው መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል። የኢትዮጵያን ታሪክ በማጥናት እና የሳይበር ደህንነት ላይ ለተመራመሩ ልጆች ሽልማት አበርክተው አበረታተዋቸዋል።

ልጆችዬ በአጠቃላይ በመድረኩ ለልጆች በጎ መሆን የመምህራን ሚና፣ የኪነጥበብ ሰዎች እና የወላጆች ሚና ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ ተነስቷል። ልጆችዬ እናንተስ ቀኑን እንዴት አሳለፋችሁ? እናንተም ጥሩ ሥራ ሠርታችሁ ለሽልማት እና ሀገራችሁን ለመጥቀም እንደምትበቁ ምንም ጥርጥር የለኝም። ልጆችዬ ለዛሬው በዚህ እናብቃ። ሳምንት በሌላ ርዕሰ ጉዳይ ለመገናኘት ያብቃን።






በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ